እ ፕ ድ
# አዲስ ዘመን
ማክሰኞ
81ኛ ዓመት ቁጥር 347 ነሐሴ 17 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






## "የዋግ ሹሞች ምድር የጀግኖች ማሕጸን፣ የቱባ ባሕል ባለቤት እና የአይበገሬዎች ተምሳሌት ነው"

- አቶ ደመቀ መኮንን
ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና
የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር




በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የዋግ ሹሞች ምድር የጀግኖች ማሕጸን፣ የቱባ ባህል ባለቤት እና የአይበገሬዎች ተምሳሌት ነው ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ተናገሩ፡፡ "ሻደይ" የልጃገረዶች በዓል በሰቆጣ ከተማ በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል፡፡

አቶ ደመቀ መኮንን ትናንት በሰቆጣ በተከበረው የሻደይ በዓል ላይ ባደረጉት ንግግር፤ የዋግ ሹሞች ምድር የጀግኖች ማሕጸን፣ የቱባ ባህል ባለቤት እና የአይበገሬዎች ተምሳሌት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አቶ ደመቀ እንደተናገሩት፤ ዋጎች በየዘመኑ ያጋጠማቸውን ከባድ ችግር በጀግንነት ማለፍ ችለዋል፤ ለዚህ ደግሞ ካለፉት ዓመታት ጀምሮ በአሸባሪው ሕወሓት ያጋጠማቸውን ከባድ ችግር በፅናትና በጀግንነት ማለፋቸው ማሳያ ነው፡፡

ባለፉት ዓመታት ሕወሓት በዋግ ሕዝብ ላይ ባደረሰው ዘርፈ ብዙ ጉዳት፣ የሕይወት መስዋዕትነት፣ የአካል ጉዳት እንዲሁም የንብረት ውድመት የደረሰባችሁ ለኢትዮጵያ የከፈላችሁት ዋጋ በመሆኑ ትልቅ ምስጋና ይገባችኋል ብለዋል፡፡

አሸባሪው ሕወሓት በጦርነትና በሕጻናት መስዋዕትነት መኖር የለመደ መሆኑን ጠቅሰው፤ አሁንም የጦርነት

"የዋግ ሹሞች ምድር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ሚዲያዎች የሚጠበቅባቸውን አገራዊ ሚና እንዲወጡ ተጠያቂነት የሰፈነበት ነጻነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተጠቆመ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ሚዲያዎች ለአገር ሁለንተናዊ እድገት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲያበረክቱ ተጠያቂነት የሰፈነበት ነጻነት ሊኖራቸው እንደሚገባ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት መምህር የሆኑት ዶክተር አጋረደች ጀማነህ ገለጹ።

ዶክተር አጋረደች ጀማነህ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዘጋጅነት ትኩረቱን በሚዲያ ላይ አድርጎ በጎንደር ከተማ በተካሄደው ፃነኛው ‹‹ስለኢትዮጵያ›› የውይይት መድረክ ላይ እንደገለጹት፤ ሚዲያዎች ትክክለኛ መረጃ ለሕዝብ እንዲደርስ በማድረግ ለአገር ሁለንተናዊ እድገት ከፍ ያለ ሚና ይጫወታሉ። ይህንን ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ተጠያቂነት የሰፈነበት ነጻነት ሊኖራቸው ይገባል።

ሚዲያዎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ - ዳኜ አበራ
ዶክተር አጋረደች ጀማነህ

## ከሰላም መንገድ መሸሽ የሕወሓት ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- በሰበብ አስባብ ከሰላም መንገድ መሸሽ የአሸባሪው ሕወሓት ተፈጥሯዊ ባህሪ መሆኑን ታሪክ ለሚያውቅ አዲስ የተፈጠረ ማንነት አለመሆኑን መገንዘብ እንደሚቻል የትግራይ ዲሞክራሲ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ ገለጹ፡፡

አቶ ሙሉብርሃን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሕወሓትን ተፈጥሯዊ ባህሪ እና የቀደመ ታሪክ ለሚያውቅ አዲስ ማንነቱ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከሕወሓት ጋር በሰላማዊ መንገድ ተወያይቶ ሰላም ማምጣት አይታሰብም፡፡

ሕወሓት ችግሮችን በሰላማዊ ውይይት የመፍታት ባህሪም ልምድ የለውም ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ ችግሮችን በጉልበት እፈታለሁ ብሎ የሚያምን ስለመሆኑ ሰሞኑን ያንጸባረቀው ተግባር ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

ወደ እርቅ እና ድርድር የሚገባ ሃይል የጸጸት እና

ከሰላም መንገድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ




ለሻደይ ያልሆነ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የመቀንጨር ችግርን ለመቅረፍ በተደረገው ርብርብ አበረታች ውጤት መመዝገቡ ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

<u>አዲስ አበባ፡</u>- በጦርነት እና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች ስርዓተ ምግብን ለማሻሻል እና የመቀንጨርን ችግር ለመቅረፍ በተደረገ ርብርብ አበረታች ውጤት መመዝገቡን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ፡፡

የ2014 በጀት ዓመት የሰቆጣ ቃል ኪዳን የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ እና ቀጣይ አቅጣጫዎች የሚመላከቱበት የከፍተኛ አመራር መድረክ በሰቆጣ ከተማ ሲካሄድ አቶ ደመቀ እንደገለጹት፤ ባለፉት ዓመታት የምግብ እና ስርዓተ ምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጡ እና መሰረታዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሊያመጡ የሚችሉ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡የመቀንጨር ችግርን ለመቅረፍ በተደረገው ርብርብ አበረታች ውጤት ተገኝቷል፡፡

በተለይ ለሰቆጣ ቃልኪዳን ተፈፃሚነት በሶስት ምዕራፍ የተከፈለ የ15 ዓመታት ፍኖተ ካርታ ተግባራዊ በማድረግ አዋጪና ዘላቂነት ያለው ርብርብ መደረጉንም አብራርተዋል።



የሰቆጣ ቃል ኪዳን የከፍተኛ አመራር መድረክ

የሰቆጣ ቃል ኪዳንን በተሟላ አግባብ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚመለከታቸው ቁልፍ የፌዴራል ተቋማት መካከል የተቀናጀ አሰራር ስርዓት መዘርጋቱ ትርጉም ያለው ውጤት ለማምጣት ጠንካራ መሰረት መጣሉን አስረድተዋል፡፡

አቶ ደመቀ በጦርነት እና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በሚገኙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ያሉ ወገኖችን በከፋ ድህነት ውስጥ ያሉ በመሆናቸው ወደፊት የቅንጅት ስራው ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ማስገንዘባቸውን ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

በመሰል ሀገራዊ ፕሮግራሞች የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ዘላቂ ሰላም በሁሉም አካባቢዎች ማረጋገጥ መንግስት ቀዳሚ ትኩረት እንደሚሰጥ እና በቁርጠኝነት ተፈፃሚ እንደሚያደርግም አረጋግጠዋል።

በመድረኩ አቶ ደመቀ መኮንንን ጨምሮ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ተሳትፈዋል።



አቶ ብርሃኑ ኩማ

# በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች በተሳተፉባቸው አካባቢዎች የትራፊክ አደጋ መቀነሱ ተነገረ

ሳሙኤል ወንደሰን

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የክረምት በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች በትራፊክ ማስተናበር ስራ ላይ በተሰማሩባቸው አካባቢዎች በተሽከርካሪ ይደርስ የነበረ አደጋ መቀነሱን የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ገለጸ።

ኤጀንሲው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ጋር በመሆን የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ በጋራ እየሰራ ነው።

የአዲስ አባባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ብርሃኑ ኩማ እንዳሉት፤ የበጎ ፍቃደኛ ወጣቶች በትራፊክ ማስተናበር ስራ ላይ በተሰማሩባቸው አካባቢዎች በተሽከርካሪ ይደርስ የነበረ አደጋ ቀንሷል።

በተሽከርካሪ አደጋ የሚጠፋውን የሰው ልጅ ሕይወትና የኢኮኖሚ ኪሳራ ለመቀነስ የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

“በበጎ ፈቃድ የሚሰራው ስራ ለራሳችንና ለወገናችን ነው” የሚሉት አቶ ብርሃኑ፤ ሁሉም ለስራው ትብብር ማድረግ እንዳለበት አስረድተዋል።

በተለይ በርካታ የህዝብ እንቅስቃሴ በሚኖርባቸው መንገዶች ላይ እየተሰራ ያለው ስራ ውጤታማ መሆኑን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ ወጣቶቹ ከመግባታቸው አስቀድሞ ከነበረው ጊዜ ጋር ሲነጻጸር በአሁኑ ወቅት አስተናባሪዎቹ ባሉበት ቦታ ምንም አደጋ አለማጋጠሙን ተናግረዋል።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በከተማዋ እያደገ መጥቷል። የክረምት በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች የትራፊክ ፍሰትን በማሳለጥ፣ የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስ፣ በደም ልገሳ፣ በአረንጓዴ አሻራ እና በተለያዩ ሙያዎች አገልግሎት ላይ እየተሳተፉ ነው ብለዋል።

በጎ ፍቃደኞቹ ያለምንም ክፍያ በራስ ተነሻሽነት የሰውን ህይወት እናድን ብለው ዝናብ እየዘነበባቸው የሚያስተናብሩትን ወንድሞቻችንን አለመታዘዝና እንደስራ ፊት ማየት ተገቢ አይደለም ያሉት አቶ ብርሃኑ፤ አሽከርካሪዎችም ሆኑ መላው ህብረተሰብ እነዚህን በጎ ፍቃደኞች አክብሮ ማለፍ ይኖርበታል ብለዋል።

የክረምት በጎ ፍቃድ ስራ ከተጀመረ ከሁለት ወራት በላይ ያስቆጠረ ሲሆን፤ በዚህም ውጤታማ ስራዎች እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በበጎ ፍቃድ ስራ ላይ የተሰማሩ ወጣቶች በበኩላቸው፤ በበጎ ፍቃድ ስራ በመሰማራት ሰዎች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ከማድረግ በላይ የሚያስደስት ጉዳይ የለም ይላሉ።

ወጣቶቹ የትራፊክ አደጋ እንዳይከሰትና በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ከትራፊክ ፖሊሶች ጋር በጋራ በመስራት የተሻለ ውጤት መገኘቱን ተናግረዋል።

ወጣቶች በሚሰጡት ትራፊክን የማስተናበር ስራ ላይ ችግር የሚፈጥሩ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ለአደጋ የሚያጋልጡ ሰዎች ናቸው።

# 23 ሺህ ነጋዴዎች የአንድ መስኮት አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸው ተገለጸ

## - የአገልግሎት መስጫ ጊዜን ከ15 ወደ 2 ነጥብ 5 ቀናት ማሳጠር ተችሏል

ውብሸት ሰንደቁ

<u>አዲስ አበባ፡</u>- የኢትዮጵያ ኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት አገልግሎት ፈቃድ ሰጪና ተቆጣጣሪ ተቋማት ላይ ተግባራዊ በማድረግ ከ23 ሺህ በላይ የወጪና ገቢ ነጋዴዎች የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻሉን ገቢዎች ሚኒስቴር ገለጸ። አገልግሎቱ የሚወስደውን ጊዜም በአማካይ ከ15 ወደ ሁለት ቀናት ተኩል ዝቅ ማድረግ ተችሏል።

በገቢዎች ሚኒስቴር የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት አገልግሎት ፕሮግራም ዳይሬክተር አቶ ሮቤል ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ባንኮችን ጨምሮ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ቁጥር 66 ደርሷል። ከ23 ሺህ በላይ ነጋዴዎችም የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል።

እንደ አቶ ሮቤል ገለፃ፤ የወጪና ገቢ ነጋዴዎች፣ አምራቾች እና ኢንቨስተሮች የንግድ ጉዳያቸውን ለማስፈፀም የበርካታ መሥሪያ ቤቶችን በር ለማንኳኳት ይገደዱ ነበር። አገልግሎቱ ከተጀመረ ወዲህ የተጠቀሱት አካላት በአጠረ ጊዜና እንግልት ሳይደርስባቸው ጉዳያቸውን ማስፈፀም እንደቻሉ ተናግረዋል።

መንግሥት ዲጅታል ትራንስፎርሜሽን ላይ በወሰደው ጠንከር ያለ እርምጃ የገቢና ወጪ ንግዱ ምቹ እየሆነ መምጣቱን ያነሱት አቶ ሮቤል፤ አገልግሎቱ የሚወስደው ጊዜ ከ15 ቀናት ወደ ሁለት ቀን ከግማሽ ዝቅ ማድረግ መቻሉን ጠቅሰው ከ23 ሺህ በላይ ነጋዴዎችና የንግድ ተቋማት በ2014 በጀት ዓመት የአንድ መስኮት አገልግሎት መጠቀም መቻላቸው የሲስተሙን አዋጭነት ያመላክታል ብለዋል።

ባንኮችን ጨምሮ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ቁጥርም 66 መድረሱን እንዲሁም በቅርቡ አዳዲስ ባንኮች እና ተቋማት እንዲገቡ በማድረግ ለዓለም አቀፍ የንግድ ሁኔታ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል ሲሉ ተናግረዋል።

ጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎት ተቋማት በተጨማሪ 24 ያህል ባንኮች የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት እየሰጡ መሆኑንም አክለው ገልፀዋል።

በ2015 በጀት ዓመት የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ቁጥር ወደ 73 ለማድረስ ይሠራል ያሉት አቶ ሮቤል፤ በተጨማሪም የተገልጋዩን እርካታ ለመጨመር፣ የቁጥጥር ሥርዓቱን ለማዘመንና የግብይት ሥርዓቱን ተገማች ለማድረግ በትኩረት ይሠራል ብለዋል። በተጨማሪም የአገልግሎት መስጫ



አቶ ሮቤል ተስፋዬ

ርዝማኔን ከ2 ቀናት ከግማሽ በታች ለማድረግ የተለያዩ መተግበሪያዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ እንደሚደረግ ነው የተናገሩት።

ከመተግበሪያዎች ውስጥ የሠራተኛ አገልግሎት ስምምነት መተግበሪያን እንደ አብነት አንስተው ማብራሪያ የሰጡት ዳይሬክተሩ፤ የሠራተኛ አገልግሎት ስምምነት መተግበሪያው በኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን አገልግሎት መስጫ ጊዜ ለመቆጣጠር የሚያገለግልና ተገልጋዩ በአጠረ ጊዜ ውስጥ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ይህ መተግበሪያ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከተገቢው በላይ ጊዜ ከተወሰደ መጀመሪያ ለባለሙያው ያሳውቃል፤ በዚህ መንገድ መልስ ካልተገኘ ለበላይ አለቆች ደረጃቸውን ጠብቆ የተፈጠረውን ችግር ያሳውቃል። በአጠቃላይም ተቋሙ ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ ከተቋሙ በላይ ላለው አካል እስከማሳወቅ የሚደርስ ነው ሲሉም ጠቁመዋል።

በዚህ አማካኝነትም አሁን በአማካይ 2 ነጥብ 5 ቀን ያለውን የአገልግሎት መስጫ ጊዜ እርዝማኔ ወደ 0 ነጥብ 5 ቀን (ግማሽ ቀን) እንዲያጥር ይሠራል። መተግበሪያው የተጠቃሚ ቅበላ ሙከራ ተደርጎበት ውጤታማ መሆኑንና በመጪዎቹ አንድ ወይም ሁለት ወራት ውስጥ ወደ ትግበራ የሚገባ መሆኑን አቶ ሮቤል አስታውቀዋል።

መንግሥት በወጪና በገቢው ንግድ እና በሌሎች ተያያዥ ዘርፎች የተተነተኑ መረጃዎችን እንዲያገኝ የሚያስችል እና ሌሎች ከሥነምግባርና ከሙስና ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚረዱ በርካታ መተግበሪያዎችም በ2015 በጀት ዓመት ወደሥራ እንደሚገቡ እንደሚያደርግ ዳይሬክተሩ ገልፀዋል።

እንደ አቶ ሮቤል ገለፃ፤ የኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት ጊዜንና ወጪን በመቆጠብ፣ ተገማችነትን በማስፈን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነትን በመጨመር እና ብልሹ አሠራሮችን በመቀነስ እንዲሁም የደንበኛን እርካታ በመጨመር ትልቅ አስተዋፅዖ አድርጓል።

አገልግሎቱ በተጓዳኝ ካስገኛቸው ጥቅሞች በተጨማሪ ከመጀመሩ በፊት የወጪና ገቢ ንግድ አገልግሎት ሥርዓት ለማስፈፀም 44 ቀናትን ይወስድ የነበረውን የተጓተተ የአገልግሎት ሥርዓት ወደ 15 ቀናት ዝቅ ማድረግ ተችሏል። በ2014 በጀት ደግሞ የአገልግሎት መስጫ አማካይ ጊዜ ወደ ሁለት ቀን ተኩል ማውረድ የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

የኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት ታህሳስ 25ቀን 2012 በይፋ ተመርቆ ሥራ የጀመረ አገልግሎት ነው።

# “ኢትዮጵያን ወደ ቀደመ ከፍታዋ እንመልሳታለን የምንለው ከተጨባጭ እውነታ ተነስተን ነው”

- ዶክተር ዐቢይ አሕመድ
የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር


ፎቶ - ዳኜ አበራ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን ወደ ቀደመ ከፍታዋ እንመልሳታለን የምንለው ከተጨባጭ እውነታ ተነስተን ነው ሲሉ የኢ.ፌ.ዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ የወጣቶች ሚና በአገር ሰላምና ዕድገት በሚል ከወጣቶች ጋር ከትናንት በስቲያ ውይይት ሲያደርጉ እንደገለፁት፤ በዓለም ተጽእኖ መፍጠሪያ መንገዶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ወታደራዊ ፣ዲፕሎማሲያዊና ኢኮኖሚያዊ አቅሞች ናቸው፡፡ቀደም ባለ ጊዜ ኢትዮጵያ በወታደራዊ ስኬት፣ በዲፕሎማሲና በኢኮኖሚ አቅሞቿ ከሌሎች የአለም አገሮች ጋር ሲነጻጸር ተጽእኖ ፈጣሪና ከፍታ ላይ የምትቀመጥ ሀገር ነበረች፡፡

ከመቶ ዓመት ወዲህ ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ እንኳን ብናይ የአፍሪካ፣ የእስያና ሌሎች አገሮች ወራሪዎችን መቋቋም አቅቷቸው በቅኝ ግዛት ስር ሲወድቁ ኢትዮጵያ በአድዋ ጦርነት አሸንፋ ነጻነቷን አስከብራለች፡ ፡ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ነጻ እንዲወጡ መክራለች ፣ደግፋለች፣ አሰልጥናለች፡፡ ይህ በወታደራዊ መስክ ከሌሎች አገራት በወቅቱ ሻል ያልን እንደነበር ያሳያል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ኮሪያና ኮንጎ ሰላም አስከባሪ ሀይል የላከችውም ከሌሎች አገሮች በወታደራዊ አቅሟ በመሻሏ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤በኮሪያና በኮንጎ የተዋጉት የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ወታደሮች ከሰለጠኑ አገራት ጭምር የተሻለ ጀግንነትና ጽናት ማሳየታቸው ዛሬም ድረስ ስማቸው እንደሚነሳ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡ ይህም ኢትዮጵያ በቀደመ ጊዜ በወታደራዊ መስክ ከፍታ ላይ እንደነበረች እንደሚያሳይ አመልክተዋል፡፡

በዲፕሎማሲ መስክም አሁን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተብሎ በሚጠራው ያኔ ሊግ ኦፍ ኔሽን በሚባለው ተቋም ብቸኛዋ አፍሪካዊት አባል አገር ኢትዮጵያ እንደነበረች አውስተው፤ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሰረትም ከሶስት መስራች አገሮች ውስጥ አንዷና ግንባር ቀደሟ ኢትዮጵያ መሆኗን ጠቅሰዋል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያን ፓስፖርት የያዘ ሰው በአጭር ጊዜ የሰለጠኑ አገራትን ጨምሮ የማንኛውም አገራት ቪዛ በቀላሉ ይመታለት እንደነበረም አውስተዋል፡፡ይህም በዲፕሎማሲው መስክ የተሻለችና ተጽእኖ ፈጣሪ መሆኗን እንደሚያሳይ ገልጸዋል፡፡

በኢኮኖሚ መስክም የዛሬ 60 ዓመት በፊት ቀይ ባህርን ተሻግረው ሀጂ የሚሄዱ የኢትዮጵያውያን ብርን እንደ ዶላር ይጠቀሙበትና ይገበያዩበት እንደነበረ አስታውሰዋል፡፡በዚያን ጊዜ በዓለም ክብር ከሚሰጣቸው አገራት አንዷ ኢትዮጵያ እንደነበረችም ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ቢያንስ እነዚህን ነገሮች ወደ ነበሩበት እንመልስ ነው ያልነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤ ኢትዮጵያውያን ያሉንን አቅሞች ሁሉ ተጠቅመን በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ከፍታው መሄድ እንችላለን ብለዋል፡፡ በተለይ ወጣቶች የቀደመውን አንድነት፣ፍቅርና መከባባርን በመመለስ ከፍታውን በአጠረ ጊዜ መመለስ እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩልም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቁ ተማሪዎች በፈቃደኝነት ከአካባቢያቸው ወጥተው ወደ ሌሎቹ የአገሪቱ ክፍሎች ሄደው ነፃ ብሄራዊ አገልግሎት የሚሰጡበት ስርዓት ለመዘርጋት መታሰቡን አመልክተው፤ በመንግስትና በግል ተቋማት የስራ ቅጥር ማስታወቂያ ሲያወጡ በዚህ ስርዓት ያለፉ ወጣቶች እንደ አንድ መስፈርት ሊታይላቸው እንደሚችል ተናግረዋል፡፡

የወጣቶች ነፃ ብሄራዊ አገልግሎት እየላላ የመጣውን አንድነታችንን የሚያጠናክርና እርስ በርስ የመተጋገዝ ባህላችንን እንደሚያጎለብት አመልክተው ፤ ወጣቶች በፈቃደኝነት 12ኛን ክፍል ሲያጠናቅቁ ወደ ሌሎች የአገሪቱ ክፍል ተንቀሳቅሰው ለህብረተሰቡ ነፃ ብሄራዊ አገለግሎት የሚሰጡበት ስርዓት ወደፊት የሚዘረጋ መሆኑን ጠቁመዋል ፡፡

አገሩን የማያውቅ ሰው አገር መምራት ያዳግተዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቀጣይ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቁ ተማሪዎች አገራቸውን ለማወቅ በፈቃደኝነት ከአካባቢያቸው ወጥተው ወደ ሌሎቹ የአገሪቱ ክፍሎች ሄደው ለህብረተሰቡ ነፃ አገልግሎት የሚሰጡበት ስርዓት ለመዘርጋት መታሰቡን ገልፀዋል ፡፡ ይህም የአንድነት ቋጠሮን እንደሚያጠብቀውና አንዱ የሌላውን ባህልና አኗኗር እንዲገነዘብ ያስችላል ብለዋል፡፡

## ክልሉ የስንዴና ሩዝ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በልዩ ትኩረት እየሰራ መሆኑን አስታወቀ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል የስንዴና ሩዝ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በልዩ ትኩረት እየተሰራ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ በክረምት መኸር ወቅት በዘር ከተሸፈነው ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት 205 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል ብለዋል፡፡

ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ከማስቀረት ባሻገር ስንዴን ወደ ውጭ ለመላክ እንደ አገር የታቀደውን እቅድ እውን ለማድረግ እንደ ክልሉ የተጀመረው ሥራ እጅግ ውጤታማ ነው ያሉት አቶ ጌቱ፤ በተመሳሳይ መልኩ የሩዝ ምርትና ምርታማነት ከዚህ በፊት ባልተመለደ መልኩ ሰፋፊ እንቅስቃሴ እየተደረገበት ይገኛል ብለዋል፡፡

በክልሉ ከዚህ በፊት የሩዝ ምርት ከአምስት ሺህ ሄክታር መሬት በላይ ሆኖ እንደማያውቅ የተናገሩት አቶ ጌቱ፣ የክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች ለሩዝ ምርት አመቺ መሆናቸውን በጥናት በመለየት በዘንድሮ ክረምት ብቻ በክልሉ ከ100 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በሩዝ መሸፈኑን አስታውቀዋል፡፡

በአገሪቱ ከውጭ ሀገር የሚደረግ የስንዴ ግዢ ማስቀረት ብቻ ሳይሆን ስንዴን ወደ ውጭ ለመላክ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማሳካት አሁን ባለው ሁኔታ በክልሉ በክረምትና በበጋ እስከ 120 ሚሊዮን ኩንታል የማምረት አቅም መኖሩን የገለጹት አቶ ጌቱ፣ በአገር ደረጃ በዓመት የሚፈለገውን 86 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ክልሉ ብቻውን ከሸፈነ በሌሎች ክልሎች የሚመረቱን ደግሞ ወደ ውጭ በመላክ በርካታ ገቢ ማመንጨት እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

በክረምት ወቅት ከሚደረገው እንቅስቃሴ ጎን ለጎን ለበጋ ስንዴ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከወዲሁ እንቅስቃሴ መጀመሩን የጠቀሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በበጋ ስንዴ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ለማልማት መታቀዱን ተናግረዋል፡፡



አቶ ጌቱ ገመቹ

የጸጥታ ችግር ያለባቸው አካባቢዎችም ቢሆን ምንም እንኳ ተጽእኖዎች ቢኖሩትም የክረምቱ እርሻ እንቅስቃሴ ጥሩ ደረጃ ላይ እንደሚገኝና ከዚህ አንጻር በእነዚህ አካባቢዎች 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ በቆሎ በተሳካ ሁኔታ መዘራቱን አመልክተዋል፡፡

እንደ አቶ ጌቱ ማብራሪያ፣ የጸጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የግብርናው እንቅስቃሴ እንዳይስተጓጎል ማዳበሪያና ምርጥ ዘር በጸጥታ አካላት ትብብር ለአርሶ አደሮች ደርሷል፡፡ሥራው ውጤታማ እንዲሆን የግብርና ባለሙያዎች እንደሌሎቹ አካላት መስዋእት በመክፈል ለአርሶ አደሩ ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በአንዳንድ ዞኖች በተለይ በቄለም ወለጋ ዞን በአሁኑ ጊዜ ህዝቡ በሁሉም አካባቢ የልማት ሥራ ላይ እንዲሰማራ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

በቂ ዝናብ ያላገኙ እንደ ቦርና፣ ሁለቱ ባሌዎችና ጉጂ አካባቢዎች የድርቁ ሁኔታ ፈታኝ ቢሆንም እንደ ሐራርጌ ያሉ በልግ ያላገኙ አካባቢዎች አሁን ላይ ዝናብ እያገኙ በመሆናቸው ቶሎ ወደ ልማት እንዲገቡ ጥረት እየተደረገ ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ አሁን በድርቁ ምክንያት ለችግር ለተጋለጡት አካባቢዎች የተለያዩ ድጋፎች እየተደረገ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

## ግድቡ የሚፈጥረውን የቱሪስት መስህብ ለመጠቀም የሚያስችል ጥናት እየተካሄደ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ታላቁ የህዳሴ ግድብ ከሚፈጥረው የቱሪስት መስህብ ስፍራ ለመጠቀም የሚያስችል ጥናት እየተካሄደ መሆኑን የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ገለጸ።

የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ኢንስቲትዩቱ የህዳሴ ግድቡ የሚፈጥረውን የቱሪስት መስህብ ለመጠቀም የሚያስችል ቅድመ ጥናት እያደረገ ነው።

የህዳሴ ግድብ ከሚሰጠው ኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫና ሌሎች ከሚሰጣቸው ጥቅሞች ባለፈ ለቱሪዝም ዘርፉ እድገት ከፍተኛ ሚና አለው ያሉት አቶ ገዛኸኝ፤ በዚህም ኢንስቲትዩቱ በህዳሴው ግድብ አማካኝነት በሚፈጠሩ ደሴቶችና ሌሎች አማራጮች ለመጠቀም የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት እንደሚያስፈልገው ተናግረዋል።

በግድቡ አካባቢ ሆቴሎች፣ በቅርብ ርቀት ከተማዎች ደግሞ የባህር ትራንስፖርት፣ የአሳ ምርትና ጀልባዎች ይኖራሉ። እነዚህ ደግሞ የቱሪስት መስህብ እንደመሆናቸው መጠን በቦታው ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ቁጥር እንዲከሰት ያደርጋል። ስለዚህ የቱሪስት አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ያስፈልጋል ብለዋል።

ቦታው በሀገራችን ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቱሪስት ያስተናግዳል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከቱሪዝም ሚኒስቴርና የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመሆን የሚፈጠረውን የህዝብ ቁጥር ማገልገል የሚችል የሰው ሀይል ለማዘጋጀት በስራ ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

አካባቢው ከፍተኛ የስራ እድል የሚፈጥር በመሆኑ ወጣቶችና ሴቶች የሚፈጠርላቸውን የስራ እድል በምን መልኩ ቢዘጋጁ ነው በራሳቸው ሀብት ማፍራት የሚችሉት የሚለውን ለማወቅ ጥናቱ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

ስለሆነም ጥናቱ በአጠቃላይ በሚፈጠሩ መዳረሻዎች ላይ ምንድን ነው ሊኖር የሚገባው? ምን አይነት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ይፈጠራሉ? ምን አይነት የሰው ሀይል ማዘጀት አለብን? ባለሃብቱ በምን ላይ ነው ተዘጋጅቶ መጠበቅ ያለበት? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል ነው ብለዋል።


አቶ ገዛኸኝ አባተ

አነስተኛ ገቢ ካለው እስከ ትልቅ አቅም ያለው ቱሪስት የሚስተናገድባቸው ሪዞርቶች፣ ሆቴሎች፣ ስፓዎች፣ ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚፈልጉትን የሰው ሀይል የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ በጎብኚነት፣ እንዲሁም በምግብ ዝግጅት፣ በእንግዳ አቀባበል፣ በቤት አያያዝና በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ስልጠና ለመስጠት የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን የሚመሰርቱ ባለሃብቶች የሚፈጠሩ እድሎችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸውና ኢንቨስት ሲያደርጉ የሚያስፈልጋቸውን የሰው ሀይል የሚያገኙበትን ሁኔታ በጥናቱ ማወቅ እንደሚቻል አስረድተዋል።

ሆቴሎች ምን ያስፈልጋቸዋል? ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ምንድን ነው የሚያስፈልጋቸው? እዛ አካባቢ የሚመጡ ጎብኚዎች በምን አይነት መንገድ መስተናገድ እንዳለባቸው ከቱሪዝም ሚኒስቴርና የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በጋራ እየሰሩ መሆኑን ተናግረዋል።

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛ ተርባይን ኃይል ለማመንጨት በመብቃቱና ሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቅ የተሰማቸው ደስታ ከፍተኛ እንደሆነም ገልጸዋል።

# ሀገር ልታጣ የነበረውን 50 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ማዳኑን ኮሚሽኑ አስታወቀ



የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት ሀገር ልታጣ የነበረውን 50 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ማዳን መቻሉን የጉምሩክ ኮሚሽን አስታወቀ።

የገቢዎች ሚኒስትሯ ወይዘሮ ዓይናለም ንጉሴ እና የኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራሮች፣ የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የ2014 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም ግምገማ እና የ2015 በጀት ዓመት እቅድ ላይ ሲወያዩ የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት በመንግስት የተሰጠውን ተልእኮ በብቃት ተወጥቷል።

ኮሚሽኑ ያከናወናቸው ተግባራት የሀገርን ኢኮኖሚ ያሳደጉ እና የህዝብን ደህንነት ያስጠበቁ ናቸው ያሉት ኮሚሽነር ደበሌ፤ ባለፈው በጀት አመት ሀገር ልታጣ የነበረውን 50 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ማዳን ተችሏል ብለዋል።

በሕገ ወጥ ንግድ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ መከላከል ዙሪያ የውስጥ አቅም፣ የህብረተሰብ እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን እንዲሁም የተቋማት ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር፣ሀገር ልታጣው የነበረውን 50 ነጥብ 4 ቢሊዮን በላይ ማዳን መቻሉን ኮሚሽነሩ መግለፃቸውን ከጉምሩክ ኮሚሽን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

በተመሳሳይ በ2014 በጀት ዓመት 5 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር የሚገመቱ የኮንትሮባንድ እቃዎችና ህገ-ወጥ ገንዘብ መያዙ ተገልጿል።

በበጀት ዓመቱ ከተያዘው 5 ነጥብ 1 ቢሊየን ብር የሚገመት የኮንትሮባንድ እቃዎች ውስጥ 4 ነጥብ 2 ቢሊየን ብር የሚገመተው የገቢ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሲሆን፤ 836 ነጥብ 6 ሚሊየን ብር በላይ የሚገመተው ደግሞ የወጪ የኮንትሮባንድ እቃዎች መሆኑ ተገልጿል።

ባለፈው በጀት ዓመት 154 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ 140 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 90 ነጥብ 7 በመቶ መሰብሰብ መቻሉን ገልጸው፤ ይህም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ28 ነጥብ 4 ቢሊዮን ወይም የ24 በመቶ ብልጫ ማሳየቱንም ኮሚሽነር ደበሌ አውስተዋል።

# ሚዲያዎች የሚጠበቅባቸውን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሚዲያ ነጻነት በተገታ ቁጥር የሕብረተሰቡ እድገት ማነቆ እንዲበዛበት በማድረግ ስልጣኔ ይገታል ያሉት ዶክተር አጋረደች፤ ነጻነት መሰጠት ያለበት ግን ከኃላፊነትና ከተጠያቂነት ጋር መሆን አለበት ብለዋል። በአንጻሩ የሚዲያን ነጻነት ያለተጠያቂነት መስጠት የሚያስከትለው አደጋ የተበታተኑ አገራትን ማየት ይገባል ብለዋል።

መረጃን በፍጥነት ለሕዝብ ማድረስ ከሚዲያዎች ይጠበቃል ያሉት ዶክተር አጋረደች፤ ይህንን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ የኮሙኒኬሽን ቢሮዎችን ጨምሮ በየደረጃው ያሉ የሥራ ኃላፊዎች መረጃ በፍጥነት መስጠት ሲችሉ መሆኑን ተገንዝበው ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

ዶክተር አጋረደች ጋዜጠኞች ተጠያቂነትን ባማከለ መልኩ ለመሥራት ሁለንተናዊ መረጃ ሊኖራቸው እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ጋዜጠኛ መረጃ ሳይኖረው ስለነጻነት ማውራት ስለማይችል መረጃ ሲጠይቅ አፋጣኝ መልስ እንዲያገኝ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንደሚገባ ጠቁመዋል።

አምባገነኖች የመረጃን ኃይል ስለተረዱ የሚዲያ ነጻነት ከረጅም ዘመናት ጀምሮ ተግዳሮቶች አሉበት ያሉት ዶክተር አጋረደች፤ በኢትዮጵያ የነጻነት ታሪክ ውስጥ ሚዲያ የራሱ ድርሻ አለው ብለዋል። አሁንም እንደ አራተኛ መንግሥት ሆኖ ሕግ አውጪውን፣ ህግ አስፈጻሚውንና ህግ ተርጓሚውን የመከታተልና የመቆጣጠር ሚናውን እንዲወጣ ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርለት እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

ሚዲያ አብሮነትን በማጠናከርና ማህበራዊ እሴቶች እንዲጎለብቱ በማድረግ በኩል የማይተካ አዎንታዊ ሚና እንዳለው አስታውሰው፤ በአንጻሩ በአግባቡ ካልተመራ ብሔራዊ አንድነትን የማናጋት፣ በሕዝቦች መካከል አለመረጋጋት የመፍጠርና የህብረተሰብን እሴት በመሸርሸር በህብረተሰቡ ዘንድ ጉዳት የመፍጠር አሉታዊ ጎን እንዳለውም መዘንጋት የለበትም ብለዋል።

ዛሬ ላይ በአገራችን በርካታ ሚዲያዎች መኖራቸው መልካም መሆኑን አንስተው፤ ብዝሃነት ላይ አተኩሮ አለመሥራት፣ መረጃ በምን መልኩ ለሕዝብ ይድረስ በሚለው ላይ አለማተኮርና ምልኡነትና ተከታታይነት የጎደላቸው ዘገባዎች የሚዲያው ችግር ሆነው ይስተዋላሉ ሲሉም ተናግረዋል:: ለሁሉም ሚዲያዎች እኩል እድል በመፍጠር በእነዚህ ጉዳዮች ላይ እንዲሠሩ ማገዝ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በባለሙያዎች በኩልም ራስን በራስ ሳንሱር ማድረግና የበሰሉ ሥራዎችን አለማቅረብ ትልቅ እንቅፋት ሆኖ እንደሚስተዋል ጠቁመው፤ በመረጃ ላይ ተመስርቶ ሥራን በማከናወንና ራስን በማብቃት ለሕዝብ የሚመጥን ሥራ መሥራት እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

# "የዋግ ሹሞች ምድር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጉሰማ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

መንግስት ሰላማዊ መፍትሄዎችን በመፈለግ የተለያዩ መንገዶችን ተጉዟል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ሕወሓት ግን የሰላም እድል እያሳጣ ለጦርነትና ለዳግም ጥፋትና ውድመት እየተንቀሳቀሰ ነው ብለዋል።

መንግስት አሁንም ቢሆን ለሰላም ያለው አቋም እንደፀና መሆኑን አረጋግጠው፤ ለሰላም አማራጭ ያለውን ኃላፊነት እስከ ጥግ ድረስ በመሄድ ኃላፊነቱን ይወጣል ነው ያሉት አቶ ደመቀ።

ካሁን በኋላ ዳግም ወደ ጦርነት ከመግባት ይልቅ ለሰላም ቅድሚያ እንዲሰጥ የትግራይ ሕዝብም የሰላም መንገዱ እንዲሳካ ግፊት እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

መንግስት ቁጭ ብለን በመነጋገር የተቋረጡ አገልግሎቶችን ለሕዝቡ መመለስ ያስፈልጋል ብሎ ለሕወሓት እድል ቢሰጥም አሸባሪው ቡድን ግን ይህን እያደረገ አለመሆኑን አስረድተዋል።

አሁንም በወረራ የያዛቸው ቦታዎች መኖራቸውን ጠቁመው፤ እነዚህን ቦታዎች በፍጥነት ለቆ ወደ ሰላማዊ ድርድር እንዲመለስ ጥሪ እናቀርባለን ብለዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ከአሸባሪ ኃይሎች የተቃጣብንን ወረራ በመቀልበስ አንድነታችንን እናጠናክራለን።

አሸባሪው ሕወሓት ባደረገው ወረራ ባለፈው ዓመት የ"ሻደይ" በዓል እንዳልተከበረ አውስተው፤ ዛሬ ግን ወረራውን ቀልብሰን በዚህ መልክ ልናከብር ችለናል ብለዋል።

የሀገር መከላከያ፣ የአማራ ልዩ ሀይል፣ ሚሊሻ እና ፋኖ እንዲሁም መላው ኢትዮጵያውያን ባደረጉት ትግል ወረራውን ቀልብሰን ሻደይን በዚህ መልክ ማክበር ችለናል፤ ለዚህም የድርሻቸውን ለተወጡ ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል ርዕሰ መስተዳድሩ። አሁንም የተቃጣብንን ወረራ በመቀልበስ አንድነታችንን እናጠናክራለን ብለዋል።

የሻደይ በዓል የልጃገረዶች የደስታ፣ የብሩህ ተስፋ በዓል ነው ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ ይህን የቱሪዝም መስህብ ለዓለም ህዝብ ማሳየት ይገባል ብለዋል።

የሻደይ በዓል በሰቆጣ ከተማ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል። በተመሳሳይም የ"አሸንድዬ" እና "ሶለል" በዓላት በላሊበላ እና በቆቦ ከተማ በደማቅ ሁኔታ መከበራቸውን ከፋናና ከአሚኮ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

# ከሰላም መንገድ መሸሽ የሕወሓት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የጥፋተኝነት ስሜት ሊሰማው ይገባል። ሆኖም ድርጅቱ የጸጸትም ሆነ የጥፋተኝነት ስሜት አይሰማውም። ኃላፊነትም መውሰድ አይችልም። እያደናገረ የትግራይ ሕዝብ የራሱን ችግር እንዳያይና ችግሩ እንዲራዘም በማድረግ ላይ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

የሕወሓት አሁናዊ እንቅስቃሴው የትግራይ ሕዝብን ከፍተኛ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ አሁን የትግራይ ሕዝብ ከፍተኛ ችግር ላይ መሆኑ እየተሰማ ነው፣ በዚህ ላይ ጦርነት ሲጨመርበት ሕዝቡን ወደአላስፈላጊና የከፋ ችግር ውስጥ ለማስገባት እየመራ ይገኛል ብለዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ እንቅስቃሴው ለመላው ኢትዮጵያውያንም ተጽእኖ ይፈጥራል፤ እንደአገር መክፈል የማይገባ ዋጋ ያስከፍላል፣ የተጀመረውን ለውጥም ወደፊት እንዳይሄድ ሊያዘገይ ይችላል፤ ነገር ግን ኢትዮጵያን ከልማት አያስቀርም ሲሉም ተናግረዋል።

ትርጉም የሌለው ጦርነት ውስጥ መግባት ተገቢ አይደለም፣ ፍላጎታችን ነገሮች በሰላማዊ መንገድ በንግግር እንዲፈቱ ነው። ነገር ግን ሕወሓት ሰላም ወዳድ አለመሆኑን እና ችግሮችን በድርድር እንደማይፈታ ማሳየት የሰላም ወዳድ ዜጋ ኃላፊነትና የሚጠበቅ ተግባር መሆኑንም።

የአለም አቀፉ ማህበረሰብ የሕወሓት ሃይል በሚሰራው ፕሮፖጋንዳ በመሸፈን የድርጅቱን ባህሪ ሳያውቀው መቆየቱን በማስታወስም፤ አሁን ሰበብ በማስቀመጥ ከሰላም ንግግር በመሸሽ ባሳየው ተንኳሽ ባህሪው የድርጅቱን ባህሪና ማንነት ሊገነዘቡ እንደሚገባም አመልክተዋል።

ትግራይ ውስጥ ጦርነቱን የለኮሰው ራሱ ሕወሓት መሆኑ ይታወቃል፤ ከጦርነቱ በኋላ የደረሱ በርካታ ጉዳቶችን ደግሞ በሌላ ሰው ያላክካል፣ ስለዚህ የዘር ማጥፋት የሚላቸው ወንጀሎች እና ችግር ፈጣሪነቱ የድርጅቱ መሆኑን የውጭ ኃይሎች መገንዘብ እንደሚገባቸው አመልክተዋል።

በሴራ ፖለቲካ የሚያምን፣ በድርድር ሰበብ ድግስ ጠርቶ በጎን የሚያርድና ተቀባይነት የሌለው ተግባር የሚፈጽም መሆኑን የአለም አቀፍ ማሕበረሰብ ሊያውቅ እንደሚገባም አመልክተዋል።

በሌላ አለም በምቾች እየኖሩ ሕወሓትን ወደ ስልጣን ለመመለስ እና ስልጣኑን ለማራዘም የሚንቀሳቀሱ የትግራይ አክቲቪስቶችም ሕወሓትን እያዳኑ የትግራይ ሕዝብን እያጠፉ መሆኑን በመገንዘብ ከድርጊታቸው ሊታቀቡ እንደሚገባም ነው የተናገሩት።

የትግራይን ሕዝብ ዋጋ እያስከፈሉት በመሆኑ ከድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል። ይልቅ እውነታውን ተገንዝበው ከለውጥ ፈላጊ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ጎን በመሰለፍ የትግራይ ሕዝብ ድምጽ በመሆን ሕወሓትን ከስርዓቱ ውጪ ሊያደርጉ ይገባል ነው ያሉት አቶ ሙሉብርሃን ።

አቶ ሙሉብርሃን እንደተናገሩት፤ ሰላም የሁሉም ቁልፍ ነው። ሰላም እና መረጋጋት እንዲኖር በተለይም የትግራይን ሕዝብ ችግር ይቀርፍ ይሆናል የሚል ተስፋ አሳይቶ ነበር።

በአንጻሩም ስጋትም ነበር። ሰላም በአንድ ወገን ጥረት ብቻ የሚመጣ አይደለም። በሌላ ወገን ያለውም ሃይል ለሰላም ዝግጁ ካልሆነ አስቸጋሪ ይሆናል። ወደኋላ ተመልሰን ብንመለከትም የፌዴራል መንግስት ወደ ጦርነት ተጎትቶ እስስኪገባ ድረስ በርካታ ጥረቶች ሲያደርግ እንደነበር ይታወሳል ብለዋል።

ችግሮች በድርድር እንዲፈቱ ተሞክሮ ነበር። ነገር ግን የተደረጉ ጥረቶች ሁሉ ከሽፈዋል። የከሸፉትም በሕወሓት ምክንያት ነው ሲሉም ሕወሓት ሰላምን ለማደናቀፍ እያደረገ ያለውን ተግባር አስረድተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ወጣቶች ኅብረብሔራዊቷን ኢትዮጵያ ወደ ከፍታዋ የመመለስ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል!

ወጣትነት ሁሉን የማድረግ ትልቅ ኃይል በሙላት የሚያዝበት ዘመን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የኃይል ባለቤትነትን የሚያኅናጽፈው የወጣትነት እድሜ ከኃይል በዘለለ ማስተዋልና ጥበብን አብዝቶ የሚሻ ስለመሆኑም ግልጽ ነው፡፡ ወጣቶች አገር ተረካቢ ናቸው ሲባል፤ ይሄን የማድረግ ኃይላቸውን ከጥበብና ማስተዋል ጋር አቀናጅተው ሀገርን ከቀደመው ትውልድ ተረክበው ለቀጣዩ ትውልድ የማስረከብ የቤት ሥራ እንዳለባቸው መገንዘብም ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም ሀገር የሚረከብ ወጣት ሀገር በመስራትና በማሻገር ሂደት ምን አውቆ መስራት እንዳለበት፤ ለዚህም አውቀው ሊጠቀሙባቸው እንዲሁም አውቀው ሊጠነቀቋቸው የሚገቡ እውነቶችን በወጉ ሊረዱ ያስፈልጋል፡፡

ከሰሞኑም እነዚህ የሀገር ተረካቢና አሻጋሪ ወጣቶች ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጋር ውይይት አድርገው ነበር፡፡ በዚህ ውይይትም ወጣቶች ጥያቄዎቻቸውን አንስተው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያና ምላሽ አግኝተዋል፤ ኢትዮጵያን በምን መልኩ ተረክበው ማሻገር እንዳለባቸውም ግንዛቤ ፈጥረው፣ የቤት ስራቸውንም ተቀብለዋል፡፡ ከውይይቱም በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ወጣቶች በሥራ ላይ የሚያተኩሩ፤ ሀገራቸውን ለማወቅ የሚተጉ፣ የሀገራቸውን ጸጋ የሚያለሙ፣ ፈጣሪያቸውን አመስጋኝ መሆን አለባቸው። ሀገራቸው ኢትዮጵያ ትልቅ እንደ ነበረች አስታውሰው ወደ ቀድሞ ከፍታዋ እንድትመለስ በኅብረብሔራዊ አንድነት ማጽናት የዚህች ድንቅ ሀገር ልጆች ግዴታ ነው"፤ ሲሉ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው መልዕክታቸውን አስፍረዋል፡፡

መሰረታዊው ነጥብና እውነታውም ይሄው ነው፡፡ ወጣቶች የአንድነት፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የመተባበርና የመሻገር እሳቤንና ግብርን ይዘው መገኘት አለባቸው፡፡ በፍቅርና በሰላም ተባብሮ በመሻገር ህሳቤና ግብር ውስጥ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታን መረዳት፤ ኢትዮጵያ ያላትን አቅም ማወቅ፤ ይሄን ተገንዝቦ የወጣትነት ጉልበትና ኃይልን ለለውጥ ማዋል፤ ይህ ሂደት በትህትናና ማስተዋል እንዲጓዝም መንገድን ለሚያቀና ፈጣሪ መታመንና ምስጋና ማቅረብ የተገባ ነው፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ መልዕክት መገንዘብ እንደሚቻለው፤ ወጣትነት ታላቅ ኃይል ቢሆንም፤ ይሄን ኃይል በፍቅር መግራት፣ በመተሳሰብ ስሜት መቃኘት፣ የሰላም እሴትን ማኅናጸፍና በፈጣሪ ታምኖ መጓዝን ይፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ወጣቱ ኢትዮጵያ የት ነበረች፤ ምንስ ነበራት፣ አሁንስ ምን አላት፣ ብዝሃነቷስ ምን ይመስላል፣ ይሄን እውነታ እንዴት አውቆና ተገንዝቦ መጠቀምና ማሻገር ይገባል፤... የሚሉ ጥያቄዎችን በመመለስ ጉዞውን መጀመር እንዳለበት የሚያሳስብ ነው፡፡

ወጣቱ ሀገር ተረክቦ የማሻገር ሚናውን ለመወጣት የመጀመሪያው ጉዳይ ሀገር ማሻገር የሚያስችለኝን ሰብዕና ለመላበስ ራሴን ከምን መጠበቅ ይገባኛል? የሚለውን መገንዘብ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የመጀመሪያው ጉዳይ አካላዊም ሆነ ስነልቦናዊ እንዲሁም አዕምሯዊ ብቃቱን ከሚጋፉ ሁነቶችና ተግባሮች ራሱን መጠበቅ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ሱስ አንዱ ወጣቱ ሊጠነቀቀው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ የአልኮል፣ የአደንዛዥ እጽ፣ የማህበራዊ ሚዲያ አሉባልታ፣ ወዘተ የዘመኑን ወጣት ከሚፈትኑትና ወደኋላ ከሚይዙት መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ የደቦ ፍትህ አካሄድንና አስፈጻሚዎችን መጸየፍ ከወጣቱ የሚጠበቅ ነው፡፡ ምክንያቱም የደቦ ፍርድ ተጓዦች ባለማወቃቸው እሳቤ ተሳስተው ሌሎችን በማሳሳት በተለይም በወጣቱ ጊዜ ላይ የራሳቸውን ሕልውናና ጥቅም የሚያጸኑ፤ ሀገርና ሕዝብን ቁማር አስይዘው የሚጫወቱ ባንዳዎች ናቸውና፡፡ እናም ወጣቱ አገር ተረካቢነቱን ሲረዳ፤ አገር አሻጋሪነቱን በተግባር ሲጀምር እነዚህን ከመሰሉ ጉዳዮች ራሱን መነጠል ይጠበቅበታል፡፡

በዚህ መልኩ የራሱን መንገድ ከለየ በኋላ፣ ሀገር በማሻገር ሂደት አቅም የሚሆነኝ ምን አለ? የሚለውን መለየት የወጣቱ ቀጣዩ ስራ ሊሆን ይገባል፡፡ የመጀመሪያው አንድነት፣ ፍቅርና መደማመጥን ስንቁ ማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀደምቶቹ አንድ ሆነው አሸንፈዋል፤ በፍቅር ሁሉን ድል ነስተዋል፤ በመደማመጥና መከባበር ታላቋን ሀገር በጋራ አቁመዋል፡፡ እናም መጀመሪያ ይሄንኑ የቀደምቶቹን እሴት ሀብቱም ስንቁም አድርጎ መያዝ ይኖርበታል፡፡

ከአንድነት፣ ፍቅርና መደማመጡ ቀጥሎ የሚመጣው ሁለተኛው ጉዳይ፣ ኢትዮጵያን ወደ ቀደመ ክብሯና ከፍታዋ ለመመለስ የሚያስችለኝ ምን ሀብት አለኝ? የሚለውን ማጤን ነው፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ተጠብቆ የኖረ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ናት፡፡ ይህ ሀብቷ በማዕድን፣ በቱሪዝም፣ በግብርናና ሌሎችም መስኮች ሳይነካ ቁጭ ያለ፤ ከተሰራበት ኢትዮጵያን ቀርቶ ለሌሎች ከፍ ማለት የሚተርፍ ሀብት ነው፡፡ ይሄን እምቅ ሀብቷን በወጉ ለይቶና በተገቢው መልኩ አልምቶ አገር ማበልጸግ፤ ወደ ቀደመ ከፍታዋ ዳግም መልሶም ለተተኪው ለማቀበል መትጋት የዚህ ዘመን ወጣት የቤት ስራ ነው፡፡

እነዚህን ሁለት አቅሞች አቀናጅቶ ከመጠቀም አኳያ ማስተዋልና ጥበብ ለወጣቱ እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡ ጥበብ ደግሞ ፈጣሪን ከማወቅና ከመፍራት ይጀምራል፡፡ ፈጣሪን ማወቅና መፍራት ሲኖር፤ ኅብረት፣ ፍቅርና መደማመጥ ይሰፍናል፤ ስለ አገርና ህዝብ ቅድሚያ ሰጥቶ መስራትን ይታደሏል፡፡ ፈጣሪን የሚያውቅ፣ የሚፈራና የሚያመሰግን ትውልድ ደግሞ ፈተና ቢበዛበት እንኳን በጽናት ይቆማል፤ መቆም ብቻም ሳይሆን ፈተናውን እንደ ዕድል ተጠቅሞ ወደ ግቡ መስፈንጠር ይችላል፡፡

በመሆኑም ወጣቱ እነዚህን ሊጠነቀቃቸውና ሊጠቀምባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ለይቶ በማወቅ፤ ኅብረብሔራዊቷን ኢትዮጵያን የማጽናት እና ወደ ቀደመ ከፍታዋ የመመለስ ኃላፊነቱን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## እንደ አሸንዳ/ሻደይ ባህላችን ፍቅራችንም ወሰንና ድንበር አይኑረው

ብስለት

በሁሉም አቅጣጫ ያሉትን የኢትዮጵያ ህዝቦች እንዳይበታተኑ ያስተሳሰሩ፤ እንዳይለያዩ ያጣመሩ፣ ጠንካራ ገመዶች በአገራችን ሁሉም ጫፎች ይገኛሉ። እኛነታችን የሚገለፅባቸው የተለያዩ በዓላት ደግሞ የኢትዮጵያዊነት ሕብር ተጠብቆ እንዲቀጥል ከሚያደርጉ ገመዶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። በዚህ ረገድ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅ ወይም ምዕራብ ላይ ሳይወሰን፤ አንዱ የሌላውን የሚያደንቅበት፣ አንዱ በሌላው ድንቅ ባህል የሚደመምበት፣ ይበልጥም አንዱ የሌላውን የሚያከብርበት፣ አንዳንዴም የአንዱ ከሌላኛው ጋር ተዋርሶና ተስማምቶ የሚገለጽባቸው በርካታ ህዝባዊ በዓላት አሉን።

ኢትዮጵያዊያን ከሰማኒያ በላይ ብሔር ብሔረሰቦች አገር ብቻ ሳትሆን፤ በየቋንቋ ባህል ቀለማቸው ተዋደውና ተዋህደው የኖሩ፣ ያሉና የሚኖሩ ስለመሆናቸው በርካታ የታሪክ፣ የባህል፣ የእምነት እና የቋንቋ ማስረጃዎች ማቅረብ የሚቻልባት ምድር ናት፡፡ ምክንያቱም አብሮ በመ ኖር ሂደት ውስጥ ተዋድዶና ተዋልዶ የተሰናሰለው ህዝብ፣ በአንድም በሌላም ባህሉን ማንነቱን ሲወራረስና ሲቀባበል ከመመልከት የላቀ እውነት አይገኝም፡፡ ከዚህም በላይ ኢትዮጵያውያን እርስ በእርሳቸው ብቻ ሳይሆን ከጎረቤት አገራት ጋር ጭምር የሚወራረሷቸውና የሚጋሯቸው ባህል፣ ቋንቋና ሌሎች ማህበራዊ እሴቶች አሏቸው፡፡

ሰሞኑን ከሚከበር አገራዊ በዓል ጋር አያይዤ አንድ ማሳያ ላንሳ፡፡ ለምሳሌ፣ ሰሜን ኢትዮጵያን ብንመለከት፤ ሰሜኑን የአገራችን ክፍል ከኤርትራዊያንን ጋር በአንድ የሚያስተሳስር ቋንቋ አላቸው፤ ከዚህም ባለፈ የጋራ የሆነ የባህል እሴት አጎልብተው ኖረዋል፡፡ የሰሜን ኢትዮጵያን ህዝቦች ከሚያስተሳስሯቸው እሴት ባህሎች ውስጥ ደግሞ በትግራይ እና በአማራ ክልሎች የሚኖሩ የትግራይ፣ የአማራ፣ የአገው፣ የኩናማ እና የኢሮብ ህዝቦች መመሳሰልና መተሳሳርን የሚያሳየው የአሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሻደይና ሶለል በዓላት ለዚህ ትስስር መገለጫ ብቻ ሳይሆኑ፤ የእውነት የተስፋ ማብሰሪያ በውብ ህብረ ቀለም የተቃኙ ናቸው፡፡

የዚህን በዓል አከባበር የተመለከተ የሩቅ አገር ሰው ሰሜኑ በሙሉ በአንድ ቋንቋ የሚናገር በአንድ አፍ የሚዘምር ነው የሚመስለው፡፡ በዚህም ከትግራይ አንስቶ እስከ ሰቆጣ የልጃገረዶች ውበትና ድምቀት ጎልቶ የሚታየው ዜማቸው ድምፅ ከዚህኛው ተራራ እስከ ወዲያኛው ያስተጋባል።

በሰሜኑ ያሉት የኢትዮጵያ ልጆች ልክ እንደ ደቡቦቹ፤ ብሎም እንደ ምስራቅ፣ ምዕራቦቹ ልጆች ከሚያለያዩዋቸው ይልቅ አንድ የሚያደረጓቸው ጉዳዮች እንደሚበዙ ከአሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሻደይ እና ሶለል የላቀ ምስክር ከወዴት ይገኛል?።

በኢትዮጵያ የሰሜኑ ክፍል ያለው ይህ ውብ ባህል የፈጠረው የትስስር እሴት ከውስጣችን ሳይበተን ከዘለቅን ኤርትራ ያደርሰናል፡፡ እናም ባህል ከአገር አገር የሚናኝ እንጂ ይህ የኔ ነው ይህ የኔ ብቻ እንደማይባል ሙሉ የሰሜን ልጃገረዶች የነፃነት በዓል የላቀ ምን ሊኖር?። ሴት ልጅ የማጀት ብቻ በምትባልበት በዛ ዘመን እንኳን አደባባይ መወጣት ነውር ከማይሆንበት ወቅቶች አንዱ የአሸንዳ/ሻደይ የበዓል ወቅት ነው።

የጭፈራውን የበዓሉን አከባበር ለተመለከተ እውነት እነዚህ ልጃገረዶች ከተለያየ ብሄረሰብ የወጡ ናቸው? ለማለት አያስደፍርም። ምናልባትም የንግግር ቋንቋቸውን ለተመለከተ የዜማቸው ምትና ቅላፄ መለያየትን ያጤነ የንግግር ቋንቋቸውና ብሔራቸው ናቸው እንዴ ሊል ካልደፈረ በፍፁም በዚህ የባህል ሰንሰለት የተሳሰሩትን የሰሜን ኢትዮጵያን ህዝቦች አንድ ከማለት በቀር በሁለት እንዳይጠራ የማድረግ ኃይል ያለው ነው፡፡

የማህበረሰቡ ትስስር፣ በማንም ጫና ወይም አስገዳጅነት ሳይሆን ከሰው የጋራ ማንነትና የጋራ ታሪክ የሚነሳ የትላንት ታሪካቸውም ሆነ የዛሬ እውነታቸው ነው፡፡ ማንም ቀመር(ፎርሙላ) ሳያዘጋጅለት ይህ በዚህ ያ በዛ ያልተባለለት በራሱ መስመር የሚፈስ ንፁህ ኩልል ያለ ውሃ ሰሜን ሙሉ የሚዞር የሚያስተሳስር እውነት፤ የፍቅርና ሰላም አውድ ነው፡፡

የሰሜኑን የአገራችንን ህዝቦች ታሪክ ስንመረምር የአሸንዳ/ሻደይ በዓላት ከላይ እስከታች እንደየአመቱ ሁኔታ፤ እንደ ምርቱ መጠን ደመቅ ፈዘዝ ይበል እንጂ፣ ለዘመናት ሥርዓቱን እንደጠበቀ ተከብሯል። አሸንዳን የመሳሰሉት የጋራ እሴቶቻችን ከቀደምት አባቶቻችን ጋር በመንፈስ የሚያስተሳስሩን ፣ ወደፊትም አብረን እንድንጓዝ የሚያደረጉን መንገድ፤ ከመንገድም አልፎ አካሄጆቻችን ጭምር ናቸው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች የሚጾሙትን የጾመ ፍልሰታ ለማርያምን መፈታት ተከትሎ ከነሐሴ አስራ ስድስት ጀምሮ ባሉ ቀናት በተለያየ እድሜ ደረጃ ያሉ ሴቶች በዋናነት ግን በወጣቶችና ልጃገረዶች የሚከበረው የአሸንዳ/ሻደይ በዓል የተስፋ ማብሰሪያ የአዲስ ዓመት መቀበያ መልካም ምኞት ማስተላለፊያ ነው።

ይህ በዓል የሴት ልጆች በተለይም ወጣት ሴቶች አንገታቸውን አቀርቅረው በሚሄዱበትና በአደባባይ ወጥተው ፍላጎታቸውን በማይገልጹበት ወቅት ሁሉ፤ በሙሉ ነጻነት ይልቁንም በጋራና በአደባባይ የወደዱትን የሚያሞጉሱበት፣ የጠሉትን ሃሳብና ተግባር በነጻነት የሚያወግዙበት ድንቅ በዓል ነው። ይህ በዓል ጦር ከማመዘዝ ይልቅ በሀሳብ ልዕልና ማመንን የሚያስተምር ነው፡፡ የአሸንዳ/የሻደይ በዓል ልክ አንገታቸውን የደፉት ልጃገረዶች ቀና እንዳሉበት ሁሉ፤ የአገራችን ህዝቦች በሀዘን ካቀረቀሩበት ቀና እንዲሉ የሚሆንበት፤ ጥልና ክርክር ቀርቶ ከሰሜን እስከ ደቡብ በፍቅር ገመድ የሚተሳሰርበት የሰው ሁሉ እንባ ታብሶ ደስታ ብቻ የሚነገስበት ዘመን ይሆንልን ዘንድ ምኞቴ ነው።

አንድ አገር ህዝቦችን ብቻ ሳይሆን ከጎረቤት ጋር የሚያቆራኘውን፣ ከአገራችን ኢትዮጵያ አልፎ ደቡባዊት ኤርትራ ውስጥ ጭምር የሚከበረው ይህ የአሸንዳ/ሻደይ በዓል ውበትና ልምላሜ የሚታይበት የአሸንዳ/ሻደይን በዓል እንደ በጎ ተምሳሌት ወስደን የኛ ልብ ውስጥ በጥላቻ የደረቀውን ተክል የምንነቅልበት፣ የፍቅር ልምላሜን የምናነግስበት ጊዜን ወደ ሕይወታችን እንድንጠራ ይሁን። ፈጣሪ ለእገሌና ለእገሌ ዝናብ፤ ለአገሌ ደሞ ድርቅ ሳይል በሙሉ እጁ ዘግኖ የሰጠንን የክረምትን በረከት እኛም የመከፋፈል የመለያየት መንፈሱን ከውስጣችን አውጥተን በፍቅር የምንለምልምበት ይሁን።

ያለምንም የሂሳብ ስሌት በመኖር ሂደት ውስጥ በባህል አንድ ሆኖ ከተሰፋው የአብሮነት ሙዳይ ውስጥ አንዷቷን የአሸንዳ/ሻደይ ሰበዝ እንምዘዝ እንጂ፤ እንመልከተው በደንብ እናስተውል ካልን ከሚያጣላን ነገር ይልቅ የሚያፋቅረን፣ ከምንናደድበት ይልቅ የሚያስደስተን ይበዛልና ቂም የጋረደውን አይናችንን በክረምት በሞሉት ወንዞቻችን ታጥበን በንፁህ መንፈስ ለእርቅ እንድንተጋ ይሁን።

እንደ አሸንዳ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬና ሶለል ውብ የባህል ህብር አገራችንም በአንድ እንድትደመር ይሁን። ተፈጥሮ አንድ ያደረገንን ፈጣሪ በአንድ ያዋደደንን ተመልከተን፣ ከእኔነት ወጥቶ እኛነት የሚለው ሀሳብ ውስጥ መግባት ተገቢ ነው። እናም ውዶቹ የአገሬ ልጆች እንደ ባህሎቻችን ሁሉ ፍቅራችን ወሰን አይኑረው፤ ድንበር አይበጅለት፤ ያለገደብ እንቀባበለው እንጂ አንግፋው፡፡ ለዛሬው አበቃሁ፤ ሰላም! ቸር ይግጠመን፤ ቸሩንም ያሰማን!

# ነፃ ሃሳብ

# እርቅ ደም ያድርቅ.....

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ያኔ ቀደም ባሉት አመታት ..እንደ አሁኑ በዘርና በጎሳ ሳንከፋፈል በፊት፤ አገራችን በእኛ እኛም በአገራችን ነበርን። እንደ አሁኑ በብሄርና በኃይማኖት ከመለያየታችን በፊት የአንድነት መገለጫችን መለያችን ነበር። አሁን ሁሉም ነገር ሌላ ነው..አንድነት ያቆነጀው ኢትዮጵያዊ መልካችን ዘርና ጎሳ፣ ብሄርና ኃይማኖት ገብቶበት ወይቧል።

ቀደም ባሉት ዘመናት ሩህሩህነት መገለጫችን ነበር፣ አይደለም እርስ በርስ ልንገዳደል ቀርቶ የተማረኩ የጠላት ምርኮኞችን አብልተንና አጠጥተን ተንከባክበን የምንሸኝ ነበርን። ዛሬ ሌላ ነን..የገዛ ወንድሙን በመግደል እና በማሰቃየት የሚኮፈስ ትውልድ አፍርተናል። በጋራ ብንኖርባት የምትበቃንን፣ በፍቅር ብንኖርባት የምትሰፋንን አንዷን ኢትዮጵያ ብዙ ቦታ ከፋፍለን እንዳትበቃን እየታገልን ነው። ተያይዞ መቆም እያለ፣ ተቃቅፎ መኖር እያለ ለመውደቅ እየተገፋፋን ነው።

ብሄሩን ትልቅ አድርጎ አገሩን ያሳነሰ፣ ዘሩን ኩሩ አድርጎ ሰውነቱን ያኮሰሰ ማህበረሰብ የኋላ ኋላ መውደቁ የማይቀር ነው። አለም ላይ ከአገራቸው ብሄራቸውን ያስቀደሙ፣ ከሰውነታቸው ዘራቸውን ያስቀደሙ ግለሰቦች ሆኑ ቡድኖች አወዳደቃቸው የከፋ እንደነበር መዛግብት ይመሰክራሉ። በታሪክ ውስጥ በነውረኝነት ተመዝግበዋል።

የእኛም በብሄር ስም የምናደርገው ያልተገባ መሯረሯጥ አንድም ለመውደቅ ከዛም በላይ ነውረኛ ታሪክ ከመጣፍ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም። ለሁላችን የምትበቃ አገር አለችን፣ በጋራ እሴት፣ በጋራ ባህል የተሳሰረ ማንነት አለን፤ በዚህ እውነት ውስጥ ጸንቶ መኖር እንጂ ለመውደቅ መገፋፋት ትርፍ የለውም።

ኢትዮጵያ አገራችን አንድ ናት..በአንድ ሀሳብ፣ በአንድ ህልም ያጸናናት የጋራ ቤታችን ናት። የአባቶቻችን አንድነት ምሰሶ ሆኖ፣ ዋልታና ማገር ሆኖ ያቆማት ናት። እኛ መጶሻ ሆነን በአንድነት ዋልታና ማገር የታነጸችውን አገራችንን ለማፍረስ መሽቀዳደም የለብንም። በብሄር ስም የምንለኩሰው እሳት መጀመሪያ የሚያቃጥለው እኛኑ ራሳችንን ነው። መርዝ መጀመሪያ ብልቃጡን እንደሚጎዳ ሁሉ ክፉ ሀሳብም መጀመሪያ ባለቤቱን ነው የሚጎዳው።

አሁን ከትናንት ተምረን ለማይጠቅመን ነገር መሮጥን ማቆም፤ በሚበጀን ነገር ላይ መትጋት ይጠበቅብናል። አሁን የሚጠቅመን በጋራ አገር ማሳደግ ነው። ከአለም ድሀ የሆነችውን አገራችንን ማልማት፣ ማሰልጠን ነው። አሁን የሚጠቅመን በቀን ሶስት ጊዜ መብላት ያልቻለ ማህበረሰባችንን መታደግ ነው። የፖለቲካ ቅራኔዎችን በእርቅ መፍታት ነው። በዘር ተኮር ፖለቲካ ያጣናቸውን በረከቶቻችንን መፈለግ ነው።

አሁን የሚጠቅመን ለወጣቱ የስራ እድል፣ ለዜጎች ደግሞ ምቹ አገር መፍጠር ነው። ህጻናት የሚያድጉባትን፣ አዛውንቶች የሚጦሩባትን አገር መገንባት ነው። አሁን የሚጠቅመን ትውልዱ የሚኮራበትን የጋራ እሴት መፍጠር ነው። ለዚህ ደግሞ ቀድመን በእርቅ ደም ማድረቅ ይጠበቅብናል። በመነጋገር ችግሮቻችንን መፍታት ያስፈልገናል። የዘር ፖለቲካ ያጠየመውን ኢትዮጵያዊነት ማደስ፤ የእኔነት አረም የበቀለበትን ሰውነታችንን ማከም ይኖርብናል።

እንዲህ ካልሆንን ንጋት አናይም። ኩርፊያና ጥላቻ ባጨለሙት ማምሻ ላይ ቆመን ንጋት መናፈቅ ሞኝነት ነው። መጀመሪያ ልቦቻችንን ለብርሀን እናዘጋጅ። መጀመሪያ አይኖቻችን ንጋት እንዲናፍቁ እናድርግ። በመጠላላት የመሹብን ንጋቶች፣ በዘር እሳቤ የዘገዩብን ተስፋዎች ከእርቅ በኋላ የሚነጉ ናቸው። እንዲነጋልን መታረቅ አለብን። መግባባት አለብን።

እስከመቼ በማይጠቅመን ነገር ላይ እየለፋን እንኖራለን? እስከመች አንድ ቦታ እየረገጥን እንደ ቀንድ አውጣ ስናዘግም እንኖራለን? የማይጠቅሙንን ስንከተል የሚጠቅሙን እያጣን እንደሆነ ለመረዳት ጊዜው አልረፈደብንም፤ ወደ ማስተዋላችን እንመለስ። አሁን ላይ ገባን ብለን የሄድንባቸው መንገዶች ያስከፈሉንን ዋጋ እናስላ። የገቡን ይሄን ያክል ካሰቃዩን በርግጥም የገቡን መሰለን እንጂ እንዳልገቡን ስለሚመሰክሩ ከዚህ መንገዳችን እንመለስ።

አሁን ከትናንት መንገዳችን ወጥተን ወደ አዲስ መንገድ እንግባ፤ ገብተውናል ያተርፉናል ባልናቸው እኔነት፣ ከፍ ያለ ራስ ወዳድነት፤ የብሄር ፖለቲካ ወዘተ .. ተሰቃይተናል። አሁንም እየተሰቃየን ነው። ገብቶናል ባልነው ዘረኝነት፣ ገብቶናል ባልነው ሀይማኖተኝነት የዘመናት እሴቶቻችንን አጥተናል። እስኪ ወደ ቀደሙት እሴቶቻችን /ወደ አልገቡን/ እንመለስ። እስኪ ወዳጣልናቸው/ወደ አልገቡን/እውነታዎች እንመልከት።

የጣልናቸው እሴቶቻችን የዘመናት ችግሮቻችን መፍትሄዎች፤ የህይወታችን አቅጣጫ ጠቋሚዎች ናቸው። ገብተውናል ባልናቸው ግን ደግሞ ባልገቡን ነውሮቻችን መሰቃየታችን ይብቃ። ያልገባን ፍቅር ነው..ያልገባን እኮ አንድነትና መቻቻል ነው። ያልተረዳነው እውነት ኢትዮጵያዊነት ነው።

እስኪ ወዳልገቡን የፍቅርና የአንድነት መንፈሶች ዞር ብለን ደግሞ እንሞክረው። እስኪ ወዳልገባን ኢትዮጵያዊነት ተመልሰን ሰላማችንን እንፈልገው፣ ሞታችንን፣ ጉስቁልናችንን እንቷ ደገው። ወዳልተረዳነው ዞረን በፍቅር ሞታችንን እንግደለው።

ብሄርተኝነት ወልዶ ባሳደገው ምናምንቴ ጭንቅላት ስናስብ ተበልጠናል። የዘር ፖለቲካ ዘርቶ ባበቀለው ሰውነት ስንመጻደቅ ተበልጠናል። ጥላቻና ዘረኝነት ባስጎነበሰው ጎባጣ ጀርባና ትከሻ እየተራመድን ተበልጠናል። አሁን ሁሉም በልጠውናል። በሁሉም ተበልጠናል። ተለያይተን የተራመድንባቸው እነዛ የመጠላላትና የመገፋፋት ዘመኖች ዛሬ ላይ በብዙ ነገር ወደ ኋላ አስቀርተውን ለውጥ ናፋቂዎች አድርገውናል።

ከዘር ፖለቲካ ወጥተን በፍቅር የምንሞትባት ኢትዮጵያ ናፍቃኛለች። ሰው እኮ በፍቅር ይሞታል..ሰው እኮ ሌላውን በማፍቀር፣ ለሌላው በመኖር ይሞታል። ነፍስ እኮ ስለሌሎች ስቃይ ታልፋለች። በኢትዮጵያ ምድር የናፈቀኝ ይሄ ነው.. በፍቅር መሞት። እስኪ በጥላቻ መሞት ቀርቶብን በፍቅር እንሙት። እስኪ በመዋደድ እንሙት፣ እስኪ በሌሎች መከራ፣ በሌሎች ስቃይ፣ በሌሎች ጉስቁልና እንሙት።

በጥላቻ መሞት ስንችል በፍቅር መሞት እንዴት አቃተን? እስካሁን ገለን የምንሞት ነን፣ ጠልተን የምንሞት ነን። የሚበጀን በፍቅር መሞት ነው። ከጥላቻ ወጥተን በፍቅር እንሙት። ህዝብ ለአገር ሲሞት አገር ለህዝብ ትሞታለች። አንዱ ለአንዱ ሲታመም ሰውነት ያኔ ዋጋ ያወጣል። ያኔ ነው አገርና ህዝብ፣ ትውልድና ታሪክ እርባና የሚኖራቸው።

ያኔ ነው እንደ አገር ወደ ፊት ለመሄድ ብርታት የምናገኘው። በፍቅር እንሙት..በሌሎች ስቃይ እንሰቃይ። የሌሎች ህመም ይመመን። የወገን ጉስቁልና ይሰማን..የፍቅር ሞት ይሄ ነው። እኔ በእናንተ ስታመም፣ እናንተ በእኔ ስትታመሙ ያኔ አገርና ህዝብ ትርጉም ያገኛል። የፍቅር ሞት ይሄንን ነው። በአንዱ ውስጥ የአንዱ መብቀል።

የፍቅር ሞት ህመም የለውም። የአንድነት ሞት ሞቶቻችንን ሁሉ የምንገልበት ጥበብ ነው። አሁን ላይ እየሞትን ያለነው በጥላቻ ሞት ነው። የጥላቻ ሞት ደግሞ ሌላ ሞት ይፈጥራል እንጂ ህይወት አይሰጥም። ሞቶቻችን የጥላቻዎቻችን ጽንሶች ናቸው። የጥላቻ ሞት ትንሳኤ የለውም። የጥላቻ ሞት ዳግም ህይወትን አይሰጥም። በፈጣሪ ፊት በክብር አያስቆምም።

ከፍቅር ርቀን ጠልተን ስንሞት በዚህኛውም አለም ሆነ በዚያኛውም አለም ትንሳኤ የለንም። ትንሳኤ ያላቸው ነፍሶች በፍቅር ኖረው በፍቅር ያለፉ ናቸው። ስለሌላው በመኖር፣ ስለሌላው በማሰብ፣ ስለሌላው በመጨነቅ በፍቅር እንሙት። ያኔ ሌላ እንሆናለን..አሁን ከሆንው ሌላ።

አገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ጥበቦች መገኛ አገር ናት። ሌላው አገር ሰላም ሲያጣ፣ አንድነት ሲርቀው ወደ ኢትዮጵያ ነበር የሚመለከተው። ኢትዮጵያን የሰላም ቀንዲል፣ የአንድነት ዋርካ አድርገው ሀገርና ህዝብ የመሰረቱ በርካቶች ናቸው። አገራችንን ተስፋ አድርገው፣ ህዝባችንን ተማምነው አገር የሆኑ እልፍ ናቸው። ዛሬ ይቺ ብዙዎችን ያስጠለለች ዋርካ አገራችን ዛፍ መሆን ባልቻሉ አገራትና ግለሰቦች ሰላሟን ስታጣ ማየት ጥያቄን ይፈጥራል።

ለሌሎች ተርፎና ተትረፍርፎ ለራስ መላ ማጣት ህመሙ በምን ቃል ይገለጻል። ሌሎችን አገርና መንግስት ያደረገች ቀዳማይት ምድር ዛሬ ዘመን ባለፈባቸው ነውረኛ ድርጊቶች ስትናጥ ማየት ከማስገረም ባለፈ ምን ሊባል ይችላል? አፍሪካን አንድ ያደረገች አገር ዛሬ ላይ በወንድማማቾች ደም ስትታጠብ ማየት ከማስቆጨትም በላይ ያማል።

አገሩን የሚወድ ሁሉ በእርቅ ደም ያድርቅ። በፍቅር ጥላቻን ይግደል። በዚች አገር ብዙ የተማጽኖ አደራዎች ተሰምተዋል። ብዙ የይቅር፣ ብዙ የእርቅ ድምጾች አስተጋብተዋል። አባቶች ተናግረዋል፣ የኃይማኖት መሪዎች አደራ ብለዋል ግን ካልገቡን ይልቅ የገቡን ልቀው ጆሮ ዳባ ብለን በራሳችን ላይ መከራ ፈጥረናል።

ካልተረዳናቸው መንፈሶች ይልቅ የተረዳናቸው የጥፋት እውነቶች ሚዛን ደፍተው ጸዳሎቻችንን ነጥቀውናል። በእርቅ ደም እንዲደርቅ፣ በፍቅር ሞት እንዲቀር ነፍሳችንን እናነቃቃ ። የሚበጀን ይሄ ነው..በእርቅ ደም አድርቀን፣ ይቅር ለእግዜር ተባብለን ወደ ፊት እንራመድ። አገር ፈርሳ መግቢያ ያለን ይመስል፣ ወገን ከድተን መጠጊያ ያለን ይመስል የጥፋት ሩጫችን አይጠቅመንም። የጥፋት ሩጫችን የሚያተርፈን የአለም መሳቂያና መሳለቂያ መሆንን ነው፤ ይህ ደግሞ የቀደመውን የአባቶቻችንን ታሪክ የሚያጎድፍ፤ ይህንንም ትውልድ ፈጽሞ የማይመጥነን ነው።

> **አፍሪካን አንድ ያደረገች አገር ዛሬ ላይ በወንድማማቾች ደም ስትታጠብ ማየት ከማስቆጨትም በላይ ያማል። አገሩን የሚወድ ሁሉ በእርቅ ደም ያድርቅ። በፍቅር ጥላቻን ይግደል። በዚች አገር ብዙ የተማጽኖ አደራዎች ተሰምተዋል። ብዙ የይቅር፣ ብዙ የእርቅ ድምጾች አስተጋብተዋል። አባቶች ተናግረዋል፣ የኃይማኖት መሪዎች አደራ ብለዋል ግን ካልገቡን ይልቅ የገቡን ልቀው ጆሮ ዳባ ብለን በራሳችን ላይ መከራ ፈጥረናል**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

# አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦች ለሥራ ዕድል ፈጠራ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በማስፋፋት ለሥራ ዕድል ፈጠራ ብሎም ሀብት መፍጠሪያ ከመጠቀም አኳያ መልካም እና አበረታች ጅምሮች መታየት ጀምረዋል። የሥራ ዕድል ፈጠራውን ውጤታማ ለማድረግም የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እገዛ እያደረጉ ሲሆን፣ የፈጠራ ስራ ሃሳብ የሚያቀርቡ ተወዳዳሪዎች ተሸላሚ የሚሆኑበት አሰራር ተዘርግቶ እየተሰራም ነው።

ሰሞኑንም የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሁለተኛውን ብሔራዊ የሥራ ጉባዔ «ዘላቂ ሥራ ለብሩህ ነገ» በሚል መሪ ሀሳብ ሁለተኛውን የስራ ጉባኤ ባካሄደበት ወቅት ከተከናወኑ ተግባሮች የፈጠራ ሥራቸውን ባቀረቡ መካከል ውድድር ተካሂዷል። የፈጠራ ስራቸውን ካቀረቡ ዘጠኝ ተወዳዳሪዎች መካከልም አሸናፊ የሆኑ ሶስት ተወዳዳሪዎች ተሸላሚ ሆነዋል።

በውድድሩ አንደኛ የወጣው የ23 ዓመቱ ወጣት ናትናኤል ታከለ ይባላል። ናትናኤል፤ በአራዳ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ አጠቃላይ ብረታ ብረትና የፋብሪካ ውጤቶች ሥራን መሰረት ካደረገ የትምህርት ክፍል የተመረቀ ሲሆን፤ ለውድድር ይዞ የቀረበውም አካል ጉዳተኞች የሚጠቀሙበት ዊልቸር ነው።

ወጣት ናትናኤል የሠራው ዊልቸር የአካል ጉዳተኞችን ድካምና እንግልት ማቃለል የሚችል፣ በሶላር የሚሠራ፣ የራሱ የሆነ ቻርጄብል ባትሪ፣ የፊት ለፊት መብራት ያለውና የብሉቱዝ ቴክኖሎጂ የተተከለለትም ነው።

ዊልቸሩ የራሱ የሆነ አፕሊኬሽን እንዲኖረውም ተደርጓል፤ ተገልጋዮች አፕሊኬሽኑን በእጅ ስልካቸው ላይ በመጫን ዊልቸሩን እስከ ሰባት ሜትር ድረስ በቀላሉ ማዘዝና መቆጣጠር የሚያስችላቸው እንደሆነ ያስረዳው ናትናኤል፤ ይህ ደግሞ የአካል ጉዳተኞችን ሕይወት ቀለል በማድረግ የተሻለ ሕይወት መምራት ያስችላቸዋል ብሏል።

ገና ልጅ እያለ ጀምሮ የፈጠራ ሥራ ይሞካክር እንደነበር የሚገልጸው ወጣት ናትናኤል፤ ተሸላሚ ያደረገውን ዊልቸር ለመስራት ያነሳሳው የ10ኛ ክፍል ተማሪ እያለ በዊልቸር የሚሄድ አካል ጉዳተኛ ከድካሙ የተነሳ ዳገት መውጣት አቅቶት መሀል መንገድ ላይ ቆሞ በመመልከቱ ነው። በወቅቱ አካል ጉዳተኛው የሚገጥመውን ችግር በዝርዝር ጠይቆ መረዳት በመቻሉና ለችግሩ መፍትሔ ያለውን ሁሉ ሲሠራ ቆይቶ በዚህ ጉባኤ ተወዳዳሪና ተሸላሚ ያደረገውን በማንዋል የሚሠራ ዊልቸር በፈጠራ ሥራ ማሳየት ችሏል።

ብዙዎች የሚጠቀሙበት ዊልቸር በሁለት እጅ የሚገፋና እጅግ አድካሚ ከመሆኑ የተነሳ አካል ጉዳተኞቹ ለተለያዩ የጤና ችግሮች የሚጋለጡ ስለመሆናቸው በመንገዱ ላይ ካገኘው አካል ጉዳተኛ የተረዳው ወጣት ናትናኤል፤ ችግሮቻቸውን ሁሉ መቅረፍ የሚያስችል የፈጠራ ሃሳብ ይዞ መቅረብ እንዳለበት በማሰብ የተለያዩ ዲዛይኖችንና ጥናቶችን በማድረግ በፈጠራ ሥራው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆነ ዊልቸር መሥራት ችሏል።

ዊልቸሩ በሞተር የሚሠራ ሲሆን፣ ልክ እንደ መኪና ፍጥነት መጨመሪያና መቀነሻ ያለው፤ 360 ዲግሪ ባሉበት ቦታ ሆነው መቆጣጠር የሚያስችል ነው። ሀዛርድና ለምሽት የሚያገለግል የግንባር መብራት እንዲሁም የራሱ የሆነ የጸሐይ መከለያም ያለውና ከፊት 10 ኪሎ ግራም፤ ከኋላ ደግሞ እስከ 70 ኪሎ ግራም የሚደርስ በድምሩ 80 ኪሎ ግራም ዕቃ ይዞ መንቀሳቀስ የሚያስችል ዊልቸር እንደሆነም ወጣት ናትናኤል አስረድቷል።

በተቻለኝ አቅም የአካል ጉዳተኞችን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ሥራ ነው የሠራሁት የሚለው ወጣት ናትናኤል፤ በቀጣይም ከውጭ ሲገባ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቀውን ዊልቸር በአገር ውስጥ በስፋት በማምረት የውጭ ምንዛሬን ለማዳን፤ ለአካል ጉዳተኞቹም ዊልቸሩን በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ ለማድረግ አቅዷል። ለአንድ ዊልቸርም እስከ 85 ሺ ብር ይጠይቃል። በአሁኑ ወቅትም ፈረንሳይ ጉራራ አካባቢ የማምረቻ ቦታ ከመንግሥት ማግኘት የቻለው ወጣት ናትናኤል፤ ለሥራ ማስጀመሪያ የሚሆን ፋይናንስ ሲያገኝ ወደ ምርት እንደሚገባ ነው የተናገረው።

ሌላኛው በፈጠራ ሥራው ተወዳድሮ ተሸላሚ የሆነው




የሽልማት ሥነሥርዓቱ በተካሄደበት ወቅት፤

የኮምቦልቻው ፉአድ መሀመድ ነው። ፉአድ፤ በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ የሜካኒካል ኢንጅነሪንግ ምሩቅ ነው። በአካባቢውም ከልጅነቱ ጀምሮ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ይሞካክር እንደነበር ገልጾ፤ የተወዳዳረበት የፈጠራ ሥራም ሊዝ ማሽን የተባለ ግዙፍ ማሽን እንደሆነ ያስረዳል። ማሽኑ አንድ ነገር ብቻ የሚሠራ ሳይሆን፣ በየትኛውም ቦታ ማንኛውንም ነገር መሥራት የሚያስችል ነው ይላል።

ሊዝ ማሽን ከስሙ ጀምሮ የማሽኖች አባት በመባል የሚታወቅ እንደሆነ ያስረዳው ፉአድ፤ ይህን ማሽን መሥራት ከተቻለ ሌሎች ማንኛቸውንም አይነት ቅርጽ ያላቸውን ማሽኖች በቀላሉ መሥራት የሚያስችል ነው ብሏል። የተለያዩ ማሽኖችን ለአብነትም ከብሎን ጀምሮ መሥራት የሚጠቅምና የተፈለገውን ቅርጽ ማስያዝም የሚያስችል እንደሆነ አስረድቷል።

ማንኛውንም መሥራት የተፈለገን አንድ ነገር በተለያየ ዲዛይን በሶፍትዌር በመሥራት በማሽኑ ማምረት ይቻላል የሚለው ፉአድ፤ የሶስተኛ ዓመት ተማሪ እያለ ሂሊኮፕተር ለመሥራት አንዳንድ አካላትን ለማሠራት በሄደባቸው የተለያዩ ቦታዎች ለትንሹ ሥራ ይጠየቅ የነበረው ዋጋ የሚቀመስ እንዳልነበረም ያስታውሳል። ይሄኔ ታዲያ ለምን ማሽኑን አልሠራም በማለት እንደተነሳሳ ይገልጻል።

በመሆኑም በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚጠይቀውን ግዙፍ ማሽን ለመሥራት ባደረገው ጥረት በፌዴራል ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት አማካኝነት ተወዳድሮ ሁለተኛ ደረጃን ማግኘት የቻለው ፉአድ፤ ማሽኑን ለመሥራት ከራሱ ከ60 እስከ 70 ሺ ብር ማውጣቱንም ይናገራል። አብዛኛው ወጪ በስፖንሰር መሸፈኑን ይገልጻል፤ አጠቃላይ ማሽኑ እስከ 200 ሺ ብር ወጪ መጠየቁን ተናግሯል።

«በግል ፈጠራ የሠራሁት ማሽን በየትኛውም ኩባንያዎች ይፈለጋል» የሚለው ፉአድ፤ በቀጣይም ይህንኑ ማሽን በማምረት ለተለያዩ ኩባንያዎች የማስረከብ ዕቅድ አለው። ማሽኑን ለማምረትም የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እየሠራ እንደሆነ በመግለጽ አሁን ለሠራው ግዙፍ ማሽን እገዛ ሲያደርጉለት ለነበሩ ለኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅና ለአማራ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ከፍተኛ ምስጋና በማቅረብ በቀጣይም እገዛቸው እንደማይለየው ያለውን ተስፋ ገልጿል።

በውድድሩ ቀርበው ተሸላሚ የሆኑት ሶስት የፈጠራ ሥራ ባለቤቶች እያንዳንዳቸው የአምስት ሺ ዶላር ወይም የ260 ሺ ብር ተሸላሚ ሆነዋል፤ ሶስቱም ያቀረቧቸው የፈጠራ ሥራዎች ወደ አገልግሎት ሊለወጡ የሚችሉ መሆናቸው ልዩ የሚያደርጋቸው እንደሆነ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በሁለተኛው ብሔራዊ የሥራ ጉባኤ መድረክ ላይ ከተካሄዱ ሁነቶች መካከል የፈጠራ ሥራ ውድድር አንዱ እንደነበር የገለጹት በሥራና ክሂሎት ሚኒስቴር የሥራ ዕድል ፈጠራ ሃሳቦች ማበልጸጊያ ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ አለምጸሐይ ደርሶልኝ፤ ውድድሩ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ወጣቶች የሚያበረታታ እንደሆነ ነው የተናገሩት።

እንደ ኃላፊዋ ገለጻ፤ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የፈጠራ ሃሳብ ላላቸው ወጣቶች ጥሪ ተደርጎ ነበር። ውድድሩ ግንቦት ወር ሊደረግ ታስቦ በተለያዩ ምክንያቶች ተገፍቶ ነሐሴ 10 ቀን 2014 ዓ.ም ተካሂዷል። ለውድድሩ 251 ወጣቶች የተመዘገቡ ሲሆን፣ ከቀረቡት የፈጠራ ሃሳቦች መካከልም የትኞቹ ችግር ፈቺዎች ናቸው? ለውጥ ማምጣትስ የሚችሉት ምን ያህሎቹ ናቸው? ምቹና የተለየ ነገር ይዘው የመጡትስ እነማን ናቸው? በሚል ተመልምለዋል። ዕድሜያቸው እስከ 29 ዓመት የሆኑ ወጣቶች የተጋበዙ ሲሆን፣ ለውድድሩ የቀረቡ መስፈርቶችን ማሟላት የቻሉ ወጣቶች እንዲወዳደሩ ተደርጓል።

በቀረበው መስፈርት መሰረት በተለያዩ ባለሙያዎች ሲመረጥ አብዛኛዎቹ ለውድድር የቀረቡ ወጣቶች መስፈርቱን ሊያሟሉ አልቻሉም ያሉት ኃላፊዋ፣ 10 ልጆች ብቻ ለውድድሩ ተመርጠው ከአስሩ ዘጠኙ የፈጠራ ሥራቸውን አቅርበው ሶስቱ ተሸላሚ ሆነዋል ብለዋል። አሸናፊዎቹም እያንዳንዳቸው የአምስት ሺ ዶላር ወይም 260 ሺ ብር ማግኘት እንደቻሉ ኃላፊዋ ጠቅሰው፤ ገንዘቡም ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን መገኘቱን ወይዘሮ አለምጸሐይ ገልጸዋል።

ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን አጠቃላይ የሥራ ዕድል ፈጠራውን በተለያየ መንገድ የሚደግፍ የውጭ ድርጅት እንደሆነ የጠቀሱት ኃላፊዋ፤ አዳዲስ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ወጣቶችና ወደ ንግድ መግባት የሚችሉ ሰዎችን ለመደገፍ ድርጅቱ በመደበው በጀት ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑን አንስተዋል።

ፈጠራ ከሌለ፣ አዳዲስ ሀሳቦች ካልመጡና ኢንተርፕራይዞች ካልተመሰረቱ የሥራ ዕድል ፈጠራ ሊኖር እንደማይችል ያመለከቱት ወይዘሮ አለምጸሐይ፤ ለዚህም የተለያዩ ድጋፎች እንደሚያስፈልግ ነው የተናገሩት። በተለይም አዳዲስ ሃሳብ ይዘው የሚመጡ ልጆች ሃሳባቸው ተደግፎ ኢንተርፕራይዝ እንዲሆኑና ለሌሎች የሥራ ዕድል መፍጠር እንዲችሉ የተለያዩ ድጋፎች እንደሚደረጉ ጠቁመው፣ ይህም የአዳዲስ ሃሳብ ባለቤቶቹ ይበልጥ እንዲነሳሱና ሌሎችም እንዲበረታቱ ያደርጋል ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ አለምጸሐይ ገለጻ፤ አዳዲስና ችግር ፈቺ ናቸው የተባሉ የፈጠራ ሃሳቦችን ወደ ተግባር ለመቀየርና በሥራ ላይ አውሎ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ እንዲቻል በየደረጃው የሚገኙ የሥራ ዕድል ፈጠራ ቢሮዎች ትልቅ ድርሻ አላቸው። በመሆኑም የፌዴራል ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ወጣቶች በክልል፣ በወረዳና በቀበሌ ካሉ ቢሮዎች ጋር በማገናኘት የተለያዩና አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን በማድረግ ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጥሩላቸው ያደርጋል።

ከዚህ ቀደምም «ብሩህ የፈጠራ ሃሳብ» በሚል በሁለት ዙር ውድድር ተካሂዶ 55 ልጆች ተሸላሚ ሆነዋል። በውድድሩ አሸናፊ የሆኑ ወጣቶችን በየጊዜው በመከታል መዳረሻቸውን ለማወቅ ጥረት ይደረጋል። በመሆኑም በርካታ ቁጥር ያላቸው ልጆች ሥራቸውን ቀጥለው ጥሩ ቦታ መድረስ የቻሉ ሲሆን፤ ከፊሎቹ ደግሞ በቦታ እጥረትና በሌሎች ምክንያቶች ሥራውን ማስቀጠል እንዳልቻሉ ይገልጻሉ። ለዚህም በአካባቢው የሚገኘው የሥራ ዕድል ፈጠራ ቢሮ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ተናግረዋል።

የተለያዩ የልማት አጋሮችን በማስተባበር የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ወጣቶች የማበረታታት ሥራ በቀጣይም የሚሠራና አሁን የተጀመረውም ቀጣይነት እንዲኖረው እንፈልጋለን የሚሉት ኃላፊዋ፤ ለአብነትም የማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ጠቅሰዋል፤ ድርጅቱ የአምስት ዓመት ፕሮግራም እንዳለውና ሁለት ዓመት ማስቆጠሩንና በቀሪዎቹ ዓመታትም ውጤታማ ሥራ እንደሚሰራም አስታውቀዋል። ይህ ሲባል ታዲያ ድጋፍ የተደረገላቸው ወጣቶች የት እንደ ደረሱ ተከታትሎ ማሳየትና መደገፍ ያስፈልጋል ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በተለይም የገጠር ወረዳና ቀበሌዎች የሚገኙ ወጣቶች የፈጠራ ሃሳብ እያላቸው ዕድሉን የማያገኙ አሉ። እነዚህ ወጣቶች ጋር ተደራሽ ለመሆን ከቀበሌዎች ጀምሮ ወደ ወረዳ ብሎም ወደ ዞን እያሉ መምጣት እንዲችሉ የማድረግ ሥራ ይሠራል፤ ለዚህም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረገ ይገኛል።

የስራና ክህሎት ሚኒስቴር በቅርቡ ባካሄደው ሁለተኛው ብሐራዊ የስራ ጉባኤ መዝጊያ ላይ በ2014 በጀት አመት የተሻለ አፈጻጸም ላስመዘገቡ ኢንተርፕርይዞች፣ የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት፣ ስራ ፈጣሪዎች እና የማእከል አገልግሎት ሰጪዎች እውቅና የመስጠት መርሀ ግብር አካሂዷል፡፡ በዚህ መድረክ ላይ የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በስራ ፈጠራ ፕሮግራም በክህሎት የበቃ የተፍታታና አምራች የሆነ ትውልድን ለመገንባት እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ የላቀ አፈጻጸም ያሳዩ ኢንተርፕራይዞችና አስፈጻሚ አካላት፣ ስራ ፈጣሪዎችና የማእከል አገልግሎት ሰጪዎች የኢኮኖሚውን መሰረት ሲጥሉ መበረታታት እንደሚገባቸው አስታውቀዋል፡፡

የስራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪያት ካሚል በበኩላቸው መድረኩ በላቀ አፈጻጸም የተሸለሙትን በዘርፉ ከተሰማሩ አካላት ልቀው የተገኙትን ተሸላሚዎች ተምሳሌት እንዲሆኑ ለማስቻል ታልሞ የተዘጋጀ መድረክ መሆኑን ጠቅሰው፣ ሽልማቱ በአነቃቂነቱ ትልቅ እሴት አካይ የሆነ ውጤት ይኖረዋል ብለን እንጠብቃለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የሥራ ስምሪትና ገበያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን፤ በአሁኑ ወቅት ቴክኖሎጂ ለሥራ ዕድል ፈጠራ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን በመግለጽ በዘርፉ የአውትሶርሲንግ፣ ፍሪላንሲንግ፣ እና ጊግ የተባሉ የሥራ ዘርፎች እየተለመዱ መምጣታቸውን ተናግረዋል። እነዚሁ ዘርፎችም ለበርካታ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደቻሉና የተፈጠሩ የሥራ ዕድሎችም የውጭ ምንዛሬ እያስገኙ እንደሆነ አስረድተዋል።

ከተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም ጋር «እንቆጳ» የተሰኘ ዲጂታል ኢንተርፕሩነርሽፕን የማስተዋወቅና የማለማመድ ሥራ በመሥራት ላይ እንደሆነ አቶ ንጉሱ ገልፀው፤ እንቆጳ ውይይት በዲጂታል መንገድ ዓለም አቀፍ ተሳታፊዎችን በማሳተፍ ሰፊ ልምድ ከማስገኘቱም በላይ ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ ሃብት በማሳየት ወደ አገሪቱ ማምጣት እና የሥራ ዕድል መፍጠር መጀመሩን አብራርተዋል።

ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን፣ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም፣ መርሲኮርፕ፣ ጂ.አይ.ዜድ፣ ጀነሬሽን አንሊሚትድ፣ ዩኒሴፍና የመሳሰሉት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በተለያዩ ዘርፎች የሥራ ዕድል ፈጠራን እያገዙ መሆናቸውንም ጠቅሰው፤ በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አቀናጅነት ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን፣ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም፣ መርሲኮርፕ፣ ጂ.አይ.ዜድ፣ ጀነሬሽን አንሊሚትድ እና ዩኒሴፍ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች «ብሩህ» ተብሎ በተሰየመ የሥራ ዕድል ፈጠራ የገንዘብ እና የባለሙያ ድጋፍ እያደረጉ እንደሚገኙም ሚኒስትር ዴኤታው ተናግረዋል።

## ወቅታዊ ትንታኔ

# ተስፋ የተጣለበት ነጻ የንግድ ቀጠና

ምሕረት ሞገስ

ነጻ የንግድ ቀጠና ማለት ምንም ዓይነት የንግድ እንቅፋት የሌለበት አካባቢ ማለት መሆኑን የኢኮኖሚ ተንታኞች ያስረዳሉ። ከሌሎች አገሮችና አካባቢዎች ያነሰ ታሪፍ ያለባቸውና አነስተኛ ታክስ የሚከፈልባቸው ናቸው፡፡ በተጨማሪ ታክስ ለመክፈል ቀላል የሆነበት አካባቢ ነው፡፡ አነስተኛ ታክስ በመከፈሉ የምርቶቹ ታሪፍ ዋጋ ቅናሽ መሆኑ መለያ ባህሪው ሲሆን፤ ንግዱን የሚያዛቡ ፖሊሲዎች ካለመኖራቸው በተጨማሪ ገበያዎቹ ጠንካራ ቁጥጥር አይደረግባቸውም፡፡

ነፃ የንግድ ቀጠና ጥቅም ሲነሳ በዋናነት የሚጠቀሰው የውጭ ኢንቨስትመንት የሚያስፋፋ ስለመሆኑ ነው። መከፈል ያለበት ታክስ እና ታሪፍ ስለሚቀነስና በዚህ መንገድ ኢንቨስት ለማድረግ ብዙ ካፒታል ስለሚገኝ የውጭ ኢንቨስተሮች ይሳቡበታል፡፡ በዚህ ምክንያት አዳዲስ ስራዎችን ለመፍጠርና የቢሮክራሲያዊ ሂደቶችን የሚቀንስ ከመሆኑም በተጨማሪ ፈጣን አገልግሎት እና ግብይት ለመፈፀም የሚያግዝ መሆኑም ይጠቀሳል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከታሪፍ ነፃ የሆነ አዲስ ዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ዕድል ከመስጠት ባሻገር፤ በአገራት መካከል የበለጠ የንግድ ትስስር እንዲፈጠር ይረዳል። በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የብሔራዊ ጥራት መሰረተ ልማት ማረጋገጫ ዘርፍ ምክትል ዴኤታ አቶ እንዳለው መኮንን እንደገለፁት፤ ነጻ የንግድ ቀጠና በአገሪቱ ያሉ ወይም ደግሞ ከዚህ ቀደም ሲሰራባቸው የነበሩ የንግድ ህጎች የማይመለከተው ሆኖ ለብቻው የተለየ አሰራርና የንግድ ማዕቀፍ ተበጅቶለት በአንድ ቦታ የሚከወን የንግድ ሥርዓት ነው፡፡ ነጻ የንግድ ቀጠና ዓለም አቀፍ የንግድ ህጎችም የሚደግፉትና አገራትም ተግባራዊ ሲያደርጉት የነበረና አሁንም እየተገበሩት ያለ አሰራር ነው፡፡

ነፃ የንግድ ቀጠና ጥቅም ብቻ ሳይሆን ጉዳትም እንዳለው ይጠቀሳል፡፡ ከሚነገሩት ጉዳቶች መካከል የበለጠ ኃይልና አቅም ያላቸውን ሰዎች የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋል። ሠራተኞችን የሚፈለገውን ያህል ብዙም የማይጠቅምና ወደ ሌሎች አካባቢዎች የስራ ፍልሰት እንዲኖር ማድረጉም ከጉዳቶቹ መካከል የሚጠቀስ ነው፡፡

ነፃ የንግድ ቀጠና ሃሳብን ተግባር ላይ በማዋል ከሚጠቀሱ አገሮች መካከል ስዊዘርላንድ፣ ኖርዌይ፣ አይስላንድን የመሳሰሉት አገሮች በዓለም ታዋቂነትን ያተረፉ ናቸው፡፡ ሜክሲኮ፣ አሜሪካ እና ካናዳን የመሳሰሉ አገራት የሰሜን አሜሪካ ነጻ የንግድ ስምምነት በማድረግ ግብይቱን ሲፈፅሙ ቆይተዋል፡፡ የደቡብ ምስራቅ እስያ ነፃ የንግድ ስምምነትም እነቻይናን ይዞ ሲሰራበት መቆየቱን ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡

ወደ አፍሪካ ሲመጣ የአፍሪካ አገራት እርስ በእርሳቸው የሚያደርጉት መደበኛ ንግድ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ ይጠቀሳል፡፡ በተለይ ባለፉት ዐሥርት ዓመታት አጠቃላይ የአገራቱ የወጪና ገቢ ንግድ ድርሻ ሁለት በመቶ ብቻ መሆኑን በማንሳት፤ የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ገበያ ቀጠና ስምምነት ይህንን ችግር ለመቅረፍ ያግዛል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡

የፀደቀው የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና አፍሪካን በገበያ ማስተሳሰር፣ በአገራቱ መካከል ንግድን ማሳደግ እና ቀጠናዊ ውሕደትን ማበረታታትና ማጠናከርን ግብ ስለማድረጉ በነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነቱ ላይ ተመላክቷል፡፡

የአፍሪካ ነጻ ገበያ ቀጠና እንደ ነጻ ንግድ ስምምነት የጸደቀው እ.አ.አ በግንቦት 30 ቀን 2019 ቢሆንም በቀጠናው ነጻ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲጀመር የተቀጠረው እ.አ.አ ሰኔ 1 ቀን 2020 ነበር፡፡ ነገር ግን የታሪፍ ድንጋጌዎች ስምምነት ላይ ያልተደረሰባቸው በመሆኑ፤ አገልግሎቶችን በተመለከተ የአዕምሯዊ ንብረት መብቶችና ኢንቨስትመንትም ሙሉ ለሙሉ ቁርጥ ውሳኔ ላይ ያልተደረሰባቸው በመሆኑ በድርድር ተጨማሪ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

ከቢቢሲ ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው ኢትዮጵያን ጨምሮ 44 የአፍሪካ አገራት መሪዎችና የአገራት ተወካዮች አህጉሪቱን በነፃ የንግድ ልውውጥ ሊያስተሳስር የሚችል ስምምነት ቀደም ሲል የፈረሙ ቢሆንም ሳይተገበር ቆይቷል፡፡ አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን አፍሪካውያንን ተጠቃሚ እንደሚያደርግና




የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነፃ የንግድ ቀጠና ግብይት ላይ በመሳተፍ ሚናውን እየተወጣ ነው፤

> ነፃ የንግድ ቀጣና መቋቋም የሥራ ዕድል የሚፈጥር ሲሆን፣ ከዚያው ጎን ለጎንም የውጭ ምንዛሬ፣ የኤክስፖርት ዕድገት፣ የኤክስፖርት ምርት ስብጥር ከማሳደግ ባሻገር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው

ለአገራት ኢኮኖሚ እድገት አስተዋፅኦ እንዳለው የተጠቀሰለት ይኸው ስምምነት በአፍሪካ አገራት መካከል ድንበር የማያግዳቸው የንግድ ልውውጦች እንዲካሄዱ እንደሚያግዝ፤ አስመጭዎች ላይ የሚጫነውን ቀረጥ በማስቀረት በአህጉሪቱ አገራት መካከል ያለውን ነፃ ዝውውር እንደሚያበረታታ ተገልጿል፡፡

ምንም እንኳ ኢትዮጵያን ጨምሮ 44 የአፍሪካ አገራት ስምምነቱ ይጠቅመናል ብለው ፈርመዋል ቢባልም፤ ጥር 2013 ዓ.ም /እ.አ.አ.ጥር 1 ቀን 2021 / ወደ ሥራ ሲገባ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነትን ከኤርትራ በቀር 54 አባል አገሮች መፈረማቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

የአፍሪካ አገራት በእኩል የዕድገት ደረጃ ላይ አለመሆናቸው ለማዕቀፉ ተፈፃሚነት ትልቅ እንቅፋት እንደሚሆን በመጥቀስ የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች ቢሞግቱም ቀድሞ ስምምነቱ በሒደት ላይ እያለ አፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና የአፍሪካ አገራትን የንግድ ልውውጥ በማሳደግ ወደ 14 ቢሊዮን ዶላር ይጨምራል ተብሎ ተገምቷል፡፡ አሁን 54 አገራት ፈርመው የተቀበሉት በመሆኑ የሚያስገኘው ትርፍ እና የአገራት ተጠቃሚነት ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል እየተተነበየ ነው፡፡

የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች እንደሚያስረዱት፤ አፍሪካን በፖለቲካ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚም የማዋሃድ ተልዕኮ ያነገበው አህጉራዊው ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት ወደ ሥራ መግባት፤ ነጻ የንግድ ቀጠናው በአፍሪካ አገራት መካከል ተመጋጋቢ የሆነ የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር፣ በአህጉሪቱ የኢንዱስትሪ ዕድገት እንዲመጣ፣ የግል ባለሃብቱ ተሳትፎ እንዲያድግ፣ ለስራ ፈጠራ እና ሚዛናዊ የንግድ ስርዓትን ለመፍጠር ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

በኮሮና ወረርሽኝ እና በሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች ተግባራዊነቱ ዘግይቶ የነበረው የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት ተግባራዊ መሆን መጀመር ለአህጉሪቱ ትልቅ ጥቅም እንደሚያስገኝ በቀጣይ በተግባር ይረጋገጣል የሚል ተስፋ ተይዟል፡፡

ኢትዮጵያ በአየር መንገዷ በኩል በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና የሚጓጓዘውን የመጀመሪያ ጭነት ከእስዋቲኒ ወደ አዲስ አበባ በማምጣት ጀምራለች፡፡ በንግድ ሚኒስቴር የባለብዙ ወገን ንግድ ግንኙነትና ድርድር ዳይሬክተር አቶ ሙሴ ምንዳዬ ነጻ የንግድ ቀጠናው ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ የሚልኩ አምራቾች ተገማችና ሰፊ የገበያ ዕድል እንዲያገኙ ያስችላል ብለዋል፡፡

'አጎአ'ን በማስታወስ ለአፍሪካ የተሰጡ የንግድ አማራጮች ቢኖሩም ዘላቂ አለመሆናቸውን ጠቅሰው፤ ይህ የንግድ ስምምነት ግን ዘላቂና አስተማማኝ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ብዙ እንደምትጠቀም ያነሱት ዳይሬክተሩ በአግባቡ ከተጠቀመች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን የምትችል መሆኑንም ያስረዳሉ፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር ዶክተር አለማየሁ ገዳ እንደሚናገሩት፤ ነጻ የንግድ ቀጠናው በአፍሪካ አገራት መካከል የሚደረገውን የንግድ ልውውጥ በ20 በመቶ ወይም በ14 ቢሊዮን ዶላር ይጨምረዋል፡፡

እንደምጣኔ ሃብት ባለሙያው ገለፃ፤ ነፃ የንግድ ቀጠና ምንም ችግር አያጋጥመውም ወይም ምንም ችግር የለበትም ለማለት አዳጋች ነው፡፡ አቶ ሙሴ ምንዳዬ በአፍሪካ ያለው የመሰረተ ልማት ሁኔታ አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ቦታዎች እየተሠሩ ያሉ የባቡር መሰረተ ልማቶች መኖራቸው ችግሩን ያቀለዋል የሚል ተስፋ እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

አገራት ከሌሎች አገራት ጋር ወይም በአህጉር ደረጃ ብቻ ሳይሆን በአንድ አገር ውስጥም ነፃ የንግድ ቀጠና ይተገበራል፡፡ በኢትዮጵያ ከሰሞኑ በድሬዳዋ ከተማ በሙከራ የተጀመረው ነጻ የንግድ ቀጠና ራሱን የቻለ የህግ ማዕቀፍ፤ ከአዋጅ ጀምሮ መመሪያና ፖሊሲ፤ እንዲሁም ራሱን የቻለ ቀጠናውን የሚቆጣጠር ተቆጣጣሪ ያለው ሆኖ የሚደራጅ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በአንድ ቦታ የተከለለና የንግድ ሥርዓቱ ከተለመደው የንግድ ሥርዓት በተለየ መልኩ የሚከወነው ንግድ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ነገር ግን የተለየ ዞን እንዳለ ተደርጎ የሚወሰድ የንግድ ቦታና ልዩ የኢኮኖሚ ዞን መሆኑን በመጥቀስ፤ በነፃ ቀጣናው የአገሪቱ የጉምሩክ ሥርዓትና አጠቃላይ ሕጎች ልማቱን ለማፋጠን በሚያስችል ሁኔታ ላልተው የሚተገበሩበት እንደሆነ በመጠቆም፤ ባለሀብቶች፣ አስመጪና ላኪዎችም ሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች በዚህ ነፃ የንግድ ቀጣና ውስጥ ገብተው ሲሠሩ የልዩ ልዩ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ በማለት ለማበረታታት ጥሪ ሲቀርብ ሰነባብቷል፡፡

ከኢትዮጵያ አንፃር በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የብሔራዊ ጥራት መሰረተ ልማት ማረጋገጫ ዘርፍ ምክትል ዴኤታ አቶ እንዳለው መንግሥት በሚፈልገው ቦታ ላይ በተለይም ከትራንስፖርትና ከሎጅስቲክስ እንዲሁም ከደረቅ ወደብ አገልግሎት ጋር ተያይዞ ቦታው የሚመረጥበት የራሱ መስፈርት እንዳለው ይናገራሉ፡፡ ይህን መስፈርት መሰረት በማድረግም የራሱ አጥር ኖሮት የተከለለ ቦታ ይኖረዋል፡፡ በዛ ቦታ ላይ የሚስተናገደው ንግድ ማንኛውም በአገሪቱ ያሉ የንግድ ህጎች የማይገዙትና ቀለል ባለ ሁኔታ የሚስተናገድ የንግድ አሰራር መሆኑን አንስተው፤ በምሳሌነትም የሰሞኗን ድሬዳዋን ገልጸዋል፡፡

የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ሲነሳ በቀጠናው ውስጥ የሚገቡ አምራቾች ከነፃ የንግድ ቀጠናው ሳይወጡ የምርት ግብአቶችን የሚያገኙበት ከመሆኑ ባሻገር፣ ከነፃ የንግድ ቀጠና ውጭ የሚያመርቱ ኩባንያዎች በግብዓትነት የሚጠቀሟቸውን ያላለቁ ምርቶች ከውጭ ሲያስገቡ እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸው ቀረጥና ታክስ በነፃ ንግድ ቀጠና ውስጥ ተግባራዊ የማይደረግ በመሆኑ የምርት ወጪ የሚቀነስ ስለመሆኑም ተጠቁሟል።

ይህም የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አምራቾች ወደ ኢትዮጵያ የነፃ ንግድ ቀጣና እንዲገቡ ትልቅ ብርታት የሚሰጥ እንደሚሆን ይታሰባል። በመሆኑም ነፃ የንግድ ቀጣና መቋቋም የሥራ ዕድል የሚፈጥር ሲሆን፣ ከዚያው ጎን ለጎንም የውጭ ምንዛሬ፣ የኤክስፖርት ዕድገት፣ የኤክስፖርት ምርት ስብጥር ከማሳደግ ባሻገር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው ፡

የመንግሥት ገቢ በማሳደግ ረገድ የራሱን ጉልህ ሚና የሚጫወት ይሆናል የሚባለው የነፃ ንግድ ቀጣና እንቅስቃሴ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና የሠራተኞች ክህሎትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና እንደሚኖረውም ይነገራል። በተጨማሪ ነፃ የንግድ ቀጣና የሚመሠረትበት አካባቢን ወይም ቀጣናን በማልማትና በማሳደግ ረገድ የሚኖረው አበርክቶ ጉልህ ስለመሆኑም ይገለጻል፡፡

በ60ዎቹ አካባቢ ሰዎች ማውራት የጀመሩለት ነጻ የንግድ ዞን፤ በእነዚህ የመጀመሪያ ዓመታት ውስጥ የአየር ማረፊያዎች እና ወደቦች አካባቢ በአጎራባች አገሮች መካከል የሁሉም ዓይነት ዕቃዎች ልውውጥ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት ታስቦ የተነሳ ፅንሰ ሃሳብ ነበር። በ80ዎቹ ግን የነፃ ንግድ ዞን ጉዳይ ልዩ ትኩረት ማግኘት የጀመረ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ከአምስት ሺህ በላይ ዞኖች በኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች እንደ ልዩ ዞኖች አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው።

እንደምጣኔ ሀብት ባለሙያዎቹ ገለፃ፤ ነጻ የንግድ ቀጠና በአፍሪካ አገራት መካከል ተመጋጋቢ የሆነ የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር፣ በአህጉሪቱ የኢንዱስትሪ ዕድገት እንዲመጣ ለማስቻል፣ የግል ባለሃብቱ ተሳትፎ እንዲያድግ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ እና ሚዛናዊ የንግድ ስርዓትን ለመፍጠር ከፍተኛ ፋይዳ ያለው በመሆኑ በልዩ ትኩረት ሊሰራበት እንደሚገባ አያጠራጥርም፡፡

ማህበራዊ

# ሴቶች




# ለሻደይ/አሽንዳ ያልሆነ ቀሚስ ....

**ሰላማዊት ውቤ**

በክረምት ወቅት ከሚበቅለው ተክል ስሙን የወረሰው በትግራይ አሸንዳ፣ በሰቆጣ ሻደይ (በኽምጣኛ ቋንቋ ‹ለምለም› ማለት ነው)፣ በላሊበላ አሸንድዬ፣ በቆቦ ሶለል ሲባል ዓይንዋ ከሚያምረው ወፍ ‹‹ዓይኒ ዋሪ›› ጋር ልጃገረዶቹን በማነፃፀር በዓሉ በአክሱም ይጠራል፡፡

አሸንዳ፣ አሸንድየ፣ ሻደይ ወይም ሶለል ከነሐሴ 16 እስከ ነሐሴ 18 ቀን ድረስ ይከበራል። ሴቶች ልጃገረዶች በልዕልና የሚታዩበት፣ በነፃነት ነግሠው የሚጫወቱበትም ነው። ከሕፃን እስከ አዋቂ የበዓሉ መገለጫ በሆኑ አልባሳትና ማጌጊያጫዎች የሚታዩት ከነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ ነው፡፡ ክብረ በዓላቱ በትግራይና አማራ ጎልተው ይታያሉ፡፡

ነሐሴ 16 ቀን ከሚከበረው የቅድስት ማርያም የፍልሰታ በዓል ጋር የተያያዘው ክብረ በዓል ከዋዜማው እስከ ማግስት ልጃገረዶች የአሸንዳ ቅጠልን አሸርጠው አደባባይ በመውጣትና በየቤቱ በመዞር እየጨፈሩና እያዜሙ ያከብሩታል፡፡ ከሕፃን እስከ አዋቂ የበዓሉ መገለጫ በሆኑ አልባሳትና መጋጊያጫዎች ተውበው ይታዩበታል፡፡ የፀጉር አሠራራቸው ከአልባሶ እስከ ግልብጭ፣ ከጋመ እስከ ድርብ፣ ጋሜ፣ ቁንጮ፣ ሳዱላና ቅርድድ ተሠርተው አደባባይ የሚውሉበት ነው፡፡ ጌጣ ጌጣቸውም ልዩ ልዩ ዓይነት ሕንቆ፣ አልቦ፣ ድሪ፣ ድኮት፣ ጉትቻ፣ ማርዳ፣ መስቀል ሲሆን፣ አለባበሳቸውም በመልጉም /ጥልፍ ቀሚስ/ ፣ ሹፎን፣ ጃርሲ ይታጀባል፡፡

ይህ የልጃገረዶች በዓል በላስታ፣ በዋግ፣ በራያ፣ በተወሰኑ የየጁ አካባቢዎች እንዲሁም በተምቤንና እንደርታ በደመቀ ሁኔታ ይከበራል። ይኼ ዓይነት የባህልም ሆነ የበዓል አከባበር ልማዱን የሚያጠፋ ከመሆኑም በላይ ለዛ እና ውበት የሌለው ነው። አሸንድዬ ልጃገረዶች በየሰፈራቸው በቡድን በቡድን ተከፋፍለው ቤት ለቤት እየዞሩ በጭፈራ፣ በዘፈን፣ በውዳሴ ሰውን እያወደሱ ለተወሰኑ ቀናት ገንዘብ ከሰበሰቡ በኋላ ድግስ ደግሰው በድልቂያ በዘፈን ድግሳቸውን የሚበሉበት የሚቦርቁበት ባህል ነው።

በዋግ ሻደይ ሲባል፣ በላስታ እና በተወሰኑ የራያ አካባቢዎች አሸንድዬና አሸንዳ፣ በየጁ እና በተወሰኑ የራያ አካባቢዎች ደግሞ ሶለል ይባላል።

በእነዚህ አካባቢዎች ልጃገረዶች አምረውና አሸብርቀው የሚታዩት ከጥምቀት ይልቅ በአሸንድዬ ወቅት ነበር። ነሐሴ ሲገባ ጀምረው ልጃገረዶች እርስ በእርስ እየተገናኙ በየእድሜ እርከናቸው ከአቻዎቻቸው ጋር ቡድን መስርተው የአሸንድየው ቀን ነሐሴ 16 እስኪደርስ ድረስ ልባቸው ስቅል ብሎ ይከርማል። ልጃገረዶቹ ለአሸንድዬው ቀን በወገባቸው የሚያስሩት የተጎነጎነ ቅጠል "የአሸንዳ ቅጠል" የሚባል ሲሆን፤ ይኼ ቅጠል በበጋ ወራት የማይገኝ ሲሆን፣ የክረምቱን ዝናብ ተከትሎ በመብቀል በአሸንድዬ ወቅት ለበዓሉ መድረሱ አስገራሚ ያደርገዋል።

የዋዜማው እለት አሸንድየውን ካለበት ቦታ ቆርጠው ካመጡ በኋላ በወገባቸው ልክ በገመድ/በማሰሪያ ከጎነጎኑት በኋላ ለጠዋት እንዳይጠወልግ ጤዛ ሳር ላይ ያሳድሩታል። በነገታው ልጃገረዶች ከቻሉ አዲስ አለበለዚያም ደግሞ የነበራቸውን ልብሶቻቸውን አጥበው ለብሰው፣ ጠጉራቸውን በሚችሉት መልኩ አበጃጅተው፣ እስከቻሉት ድረስ በሚገባ አምረው እና ተቆነጃጅተው አሸንድዬ፣ ወፌይላላ እያሉ ሲጨፍሩ ሲዘሉ ይውላሉ።

ልጃገረዶች ቀን ቀን የተጎነጎነውን አሸንድዬ ወገባቸው ላይ አስረው በየመንደሩ እየዞሩ የሚጨፍሩ ሲሆን፤ ማታ ማታ ደግሞ የተጎነጎነውን አሸንድዬ ከወገባቸው በመፍታት በሚቀጥለው ቀን ላለው ጭፈራ እንዳይጠወልግ ጤዛ ውስጥ ያሳድሩታል።

አሸንድዬ ባይ ልጃገረዶች ወደሚያወድሱት ቤት ሲገቡ አውጫዋ ልጅ <<እሜቴ አሉ ደህና ወይ>> ስትል ተቀባዩቹ <<አሉ እንጂ ግቡ ይላሉ እንጂ>> ብለው በህብረት ያዜማሉ። ከዚያ አሸንዳዬ፣ ወፌ ይላላ እየተባለ ዜማው/ዘፈኑ ስጦታውን እስኪቀበሉ ድረስ የተለያዩ የውዳሴ ስንኞች እየተቋጠሩ እንደሚከተለው ይቀጥላል።

**አሸንዳዬ**
**አሃ**
**አሸንዳ ሆይ**
**ሽርግፍ አትይሞይ**
**አሸንዳ ሙሴ**
**ፍስስ በይ በቀምሴ**

**አበሙሴ አንቺ አበሙሴ**
**ሽርግፍ በይ በቀሚሴ**

**አሸንዳዬ አሸንዳ አበባ**
**ጠብ እርግፍ እንደ ወለባ**

**ምድር ጭሬ ጭሬ አወጣሁ ማሰሮ**
**እሰይ የእኔ እመቤት ድልድል ወይዘሮ**

**ከሰፌድ ላይ አተር ኮለሌ ኮለሌ**
**የኔማ እሜቴ አንገተ ብርሌ**

ወዘተ ግጥሞችና ስንኞች እየተደረደሩ ጨዋታው ከደራ በኋላ ስጦታውን ሲያገኙ

ምስጋናቸውን እንደሚከተለው

**ትሻል እሜትዬ ትሻል**
**ይሻል ጌትዬው ይሻል**

በማለት ይገልጣሉ።

በልጅነታችን ልጃገረዶች አሸንድዬ ሲሉ አንዳንዶቻችን ወንዶቹ ከልጃገረዶቹ ወገባቸው ላይ ያለውን አሸንዳ መንጨት በጣም ከሚያስደስተን ነገር አንዱ ነበር። በተለይ ከሰፈራቸው ውጭ የሚመጡትን ልጃገረዶች አሸንዳ በመንጨት ባዶ ማስቀረት አንዱ የጨዋታው ገጽታ ነው። አንዳንድ አሸንድዬ ባይ ቡድኖች ከእንደዚህ አይነት ነገር ራሳቸውን ለመከላከል ዱላ እና ጅራፍ ይዞ ነጭዎችን የሚከላከል ፈርጠም ያለ ልጅ ያስከትላሉ።

በዚህን ጊዜ አሸንድየውን የሚነጭ ልጅ ካለ ጦርነቱ የሚሆነው ከባለ ዱላው እና ከባለ ጅራፉ ጋር ነው። አንዳንዴም ወንዶች የሰፈራችውን ልጃገረዶች አሸንድዬ ሌሎች እንዳይነጩባቸው ለመጠበቅ ተከትለዋቸው ይጓዛሉ፡፡

ከተለያየ ሰፈር የመጡ የልጃገረዶች ቡድኖች ሲገናኙ በሜዳየ መጣሽ ተባብለው አሸንድያቸውን ይነጫጫሉ። በአንዳንድ አካባቢዎች ልጃገረዶች ላይ ቀበሌና ታች ቀበሌ በሚል ከሁለት ቡድን ተከፍለው ቅልጥ ባለ ሁኔታ አሸንድየ ሲጫወቱ ይውላሉ፡፡ ሆኖም ሴቶች ልጅ ሲወልዱ አሸንድዬ መጫወት ያቆማሉ፡፡ ምክንያቱም ሴት ልጅ ካገባችና ከወለደች ጨዋታው ላይ መሳተፍ ስለማትችል ነው። ልጃገረዶቹም ለትዳራቸው የሚያጫቸው ሰውም በግላጭ የሚያያቸው በዚህ የአሸንድዬ ወቅት ነው።

አሸንድዬ ሲጨፍሩ በቤተሰብ ባል ታጭቶላቸው ድሮ ዳቦና በግ ከአማቶቻቸው በእለቱ የሚመጣላቸውም አይጠፉም። የአሸንድዬ ወቅት ደስ ከሚሉ የዓመቱ ጊዜያት አንዱ ነው፤ የክረምቱ ዝናብ እየቀለለ መሄዱ፣ ክረምቱ የሚፈጥረው ልምላሜ የተዋበ መሆኑ፣ የወንዞቹ ጥራት እና በየቦታው ከሚፈነዱት ምንጮች ጋር ተያይዞ የሚማርክ ጊዜ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የአሸንድዬው ጨዋታ፣ የቡሄ፣ የሆያሆየው ድግስ ወዘተ ጋር ተደምሮ ልዩ ጊዜ ያደርገዋል።

**«አሸንዳዬ አሸንዳ አበባ**
**ጠብ እርግፍ እንደ ወለባ»**

በየቤቱ፤ በየመዝናኛ ቤቱ፤ አንዳንዴም በየቢሮው ጭምር እየዞሩ የሚያማምሩት ልጃገረዶች ባህላዊ ጨዋታቸው በተለመደባቸው የአገሪቱ አካባቢዎች ሲደረድሩት ከሰሙት ግጥም የአማራ ክልል አባይ ማዶ አካባቢ ነዋሪዋ ወይዘሮ ካሰች በዜ በቃላቸው መያዝ የቻሉት ስንኝ ነው፡፡ ወይዘሮዋ ስለተጫዋቾቹ ውበት እንደሰጡን የአሸንዳዬ ጨዋታ ሳቢና ማራኪ ነው ፤ ልብም ላይ ሀሴት ይፈጥራል፡፡ አለባበሳቸውና ፀጉር አሰራራቸው ልዩ ነው፡፡ በአግራሞትም ያስደምማል። በተለይ ወገባቸው ላይ ያገለደሙት አረንጓዴ ልምላሜ ያልተለየው ጉንጉን የአሸንዳ ቅጠል በተለየ ሁኔታ እንዲደምቁና እንዲታዩ አድርጓቸዋል፡፡

ጨዋታው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን መዲና አዲስ አበባና በተለያዩ በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች እየተለመደ መምጣቱን አስተውለዋል፡፡ መለመዱ ባህሉን ያስተዋውቅና እንዳይዘነጋ ያደርጋልም የሚል ዕምነት አላቸው፡፡ ወይዘሮ ካሰች በዜ እንደነገሩን ጨዋታው አንድ ዓይነት ቢሆንም በተለያየ ስያሜ በመጠራት ይታወቃል፡፡

ለምሳሌ እኔ በተወለድኩበት ሰሜን ወሎ ላሊበላ አካባቢ አሸንድዬ በመባል ነው የሚጠራው ብለውናል። በዚሁ እሳቸው በተወለዱበት አካባቢ በሚገኘው ዋግ ኸምራ ዞን አካባቢ ደግሞ ሻደይ ተብሎ እንደሚጠራም ወይዘሮ ካሰች ነግረውናል፡፡ በዚሁ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ውስጥ በሚገኘው ቆቦ አካባቢ ሶለል ተብሎ የሚጠራበት ሁኔታ እንዳለም አጫውተውናል፡፡

አጎራባች በሆነችው ትግራይ ክልል አሸንዳ በዚሁ ክልል አክሱም አካባቢም የጨዋታውን ተዋናይ ልጃገረዶች ዓይንዋ ከሚያምረው ወፍ ‹‹ዓይኒ ዋሪ›› ዓይነ ዋሪ ተብሎ እንደሚጠራ አውግተውናል፡፡ ጨዋታው በልጃገረዶቹ አማካኝነት ከነሐሴ 16 እስከ ነሐሴ 18 ቀን ድረስ በሁሉም አካባቢዎች የሚካሄድ መሆኑ እንደሚያመሳስለው ወይዘሮ ካሰች አረጋግጠውልናል፡፡ እንደሳቸው ጨዋታው ሰላማዊ ነው፡፡ ፀብ፤ ክርክር ሌሎች ዝባዝንኬዎች ስለሌሉትና በሳቅ በጨዋታ የታጀበም በመሆኑ በአንድነት አብሮ የመኖር መስተጋብርን ለማጠናከር ይረዳል፡፡ አሁን እየተለመደ እንደመጣው በዋና ዋና የአገሪቱ አካባቢ በሚገኙ ከተሞች እየሰፉ መምጣቱም ባህሉን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሳይበረዝ ጠብቆ ከማስተላለፍ ባሻገር ፍቅርን ያጠናክራል፡፡

እኔ በምኖርበት አካባቢ ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ ሳይሆን ለሻደይ ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ ነው የሚባለው ሲሉ ስቀው በማሳቅ አስተያየታቸውን ይጀመራል ወይዘሮ አሰፉ ዋቅሹም ጨዋታው ለዛ ያለውና የፍቅር መገለጫ እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡ በልጅነታቸው ለአቅመ ሄዋን እስኪበቁ ጨዋታውን ተጫውተው ማለፋቸውንም ያወሳሉ፡፡ እኛ አምረንና አሸብርቀን የምንታየው በአሸንድዬ ወቅት ነው የሚሉት ወይዘሮ አሰፉ ለጨዋታው ዝግጅት የሚያደርጉት ገና ከነሐሴ መግቢያ ጀምሮ መሆኑንም አውግተውናል፡፡ ከነሐሴ ወር ጀምረን በዕድሜ እኩያ በእኩያ የሆነው ተፈላልገን እርስ በእርስ እንገናኛለን፡፡ ቡድንም እንመሰርታለን፡፡

የሻደዩ ቀን ነሐሴ 16 እስኪደርስ ድረስ ልባችን ስቅል ብሎ ይከርማል። ለሻደዩ ቀን በወገባችን የምናስረውን የተጎነጎነ ቅጠል "የሻደይ ቅጠል" ፍለጋ ስንባዝን ነው የምንከረመው፡፡ ቅጠሉ በቅርብም የሚገኝ ቢሆንም ከቅጠል ቅጠል ውበት ያለውን ለመምረጥ ከአካባቢያችን ብዙ ኪሎ ሜትር ርቀን የምንጓዝበት ጊዜም ብዙ ነው። ይኼ አረንጓዴ ልምላሜን የተላበሰው ቅጠል በበጋ ወራት በፍፁም አይገኝም፡፡ ክረምት ላይ ግን በሁሉም አካባቢዎች ይበቅላል፡፡ ሆኖም አረንጓዴ የተላበሰው ልምላሜው ድምቀት ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ እርቀን በመሄድ ጊዚያችንን የምናጠፋውም ለዚህ ነው፡፡ ከሚገርመኝ የክረምቱን ዝናብ ተከትሎ በመብቀል ልክ የበጋውን ወራት ተከትላ ብቅ እንደምትለው እንደ አደይ አበባ ሁሉ ቅጠሉ በሻደይ ወቅት ለበዓሉ መድረሱ ነው ብለውናል፡፡ መልካም በዓል!!!

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

**በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን በ1960ዎቹ በተለይም በክረምቱ ወራት ታትመው ስንባብ የበቁ አትሞች ስመቃኘት ሞክረናል፡፡ በክረምቱ ችግኝ ተከላን በሚ መለከት የተሠራን አንድ ዘገባ እንዲሁም በክረምቱ የመብረቅ አደጋ በአንድ ቤት ላይ ባደረሰው አደጋ በሕይወትና በንብረት ላይ ያስከተለውን ጉዳት የሚነግረን ዘገባም ተካቷል። በወቅቱ ያልተለመዱ ወይም ትንግርት የሆኑ ክስተቶችን ያካተተ ዘገባም እነሆ ብለናል።**

### መብረቅ የ፬ ሰዎች ሕይወት አጠፋ

**አገረ ሕይወት (ኢ/ዜ/አ/)** በጅባትና ሜጫ አውራጃ ግዛት በኖኖ ወረዳ በማሩ ኢሉ ም/ወረዳ ግዛት ጨንዶ ከሚለው ቀበሌ ባለፈው ወር መጨረሻ ግንቦት ፳፱ ከቀኑ ፲ ሰዓት ላይ በጣለው ኃይለኛ ዝናብ የወደቀው መብረቅ የ፬ ሰዎች ሕይወት አጠፋ።

ይኸው የአቶ ደጀኔ ገብሬ ቤት የወደቀው መብረቅ በቤቱ ውስጥ የነበሩትን ተፈራ ደጀኔ፤ ዳመኑ ደጀኔ፤ ቡሎ ካብትህ ይመርና ቦጋለ ገብረየስ የተባሉትን ሰዎች ሲገድል፤ የሟቾቹንም አስከሬን አስከትሎ በዚሁ አደጋ ከቤቱ ጋር አብሮ መቃጠሉን የወረዳው ግዛት ዋና ጸሐፊ አቶ ተስፋዬ ቡሉ ገልጠዋል፡፡

(ሰኔ 10 ቀን 1961 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### እመት አበቡ በ፩ ጊዜ ፭ ልጆች ወለዱ፤

**ደብረ ብርሃን፤ (ኢ.ዜ.አ)** በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በተባለው ቀበሌ ኗሪ የሆኑት እመት አበቡ አያኔ ግንቦት ፳፯ ቀን ፷፩ ዓ/ም/ ፫ ወንዶች ልጆችና ፪ ሴቶች ልጆች ተገላገሉ፡፡ ከነዚሁ ከተወለዱት ፭ ህፃናት መካከል ፪ቱ ሲሞቱ፤ ፫ቱ ግን በደኅና ሁኔታ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን የወረዳው ግዛት ዋና ፀሐፊ አቶ አበባ ለማ ገልጠዋል፡፡

እነዚሁ የተወለዱት ህፃናት የሚረዱት በክፍሉ መልከኛ በባላምባራስ አንዳርጋቸው ዓዲ መሆኑን ዋና ጸሐፊው ጨምረው አስረድተዋል፡፡ የዲርማ ቀበሌ የሚገኘው በሞረት ወረዳ በኘአ ም/ወረዳ ግዛት ነው፡፡

(ሰኔ 1 ቀን 1961 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### ስጐጃም ጠቅላይ ግዛት ፪ ሚሊዮን የዛፍ ችግኝ ተዘጋጅቷል

**ደብረ ማርቆስ፤ (ኢ-ዜ-አ-)** የጐጃም ጠቅላይ ግዛት እርሻ ጽ/ቤት በዚህ ዓመት በ፰ የእርሻ ጣቢያዎች ያለማቸውን ፪ ሚሊዮን ፩ሺህ ፩፻፴፫ የዛፍ ችግኞች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ማስተከል ጀመረ፡፡

በዚሁ መሠረት በመቻከል ወረዳ በአማኑኤል ከተማ የሚኖረው ሕዝብ ሐምሌ ፲ ቀን ፷፩ ዓ/ም/ በወረዳው ገዢ በአቶ አያሌው አብዲ አማካይነት በከተማው መንገድ ግራና ቀኝ ፬ሺህ ፳፻ ልዩ ልዩ ዓይነት ዛፎችን ተከሏል፡፡ እነዚህ የዛፍ ችግኞች በደምበጫ የችግኝ ማልሚያ ጣቢያ የለሙ መሆናቸው ታውቋል፡፡

በጠቅላላውም ችግኞቹ የለማባቸው የእርሻ ጣቢያዎች ደብረ ማርቆስ፤ ደጀን፤ ደምበጫ፤ ፍኖተ ሰላም፤ ቡሬ፤ ዳንግላ፤ አንዳሳና ቢቸኛ ጣቢያዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ጣቢያዎች የለሙት ፲፬ ዓይነት የዛፍ ችግኞች ቀይና ነጭ ባሕር ዛፍ፤ ዋንዛ፤ የሐገር ውስጥና የውጭ አገር ጥድ፤ አሜድል፤ ፓይንፓቼላ፤ ፓይን ለዲያታ፤ አርዘሊባስ፤ ዝግባ፤ ኮሶ፤ ክትክታ፤ ግራና ፌጮ የተባሉ ዘሮች መሆናቸውን የጠቅላይ ግዛቱ የርሻ ሥራ ዲሬክተር አቶ ደፋር ታፈሰ ገለጡ፡፡

(ሰኔ 15 ቀን 1961 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### የሽክላ ፋብሪካ በሚሊዮን ብር ተሠራ

**አዲስ አበባ፤ (ኢ-ዜ-አ-)** በ፩ ሚሊዮን ፳፻ ሺህ ብር ካፒታል የተሠራው የአዲሱ ሸክላ አክሲዮን ፋብሪካ በሚመጣው ታኅሳስ ወር ሥራው ይጀምራል።

በሙሉ አውቶማቲክ የሆነ የሸክላ መሣሪያ የሚኖረው የአዲሱ ሸክላ ፋብሪካ ሥራው በሚጀምርበት ጊዜ በአንድ ቀን 70, 000 ጡቦች (ሸክላዎችን) እየሠራ ለገበያ የሚያቀርብ መሆኑን ሚስተር ዳናሰድ ጂ ሀን ካላፌ የፋብሪካው ሥራ ዋና መሐንዲስ ገልጠዋል፡፡

የፋብሪካው ሕንፃ ሥራ ከተጀመረ ስምንት ወሩ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ ከጠቅላላው የፋብሪካ በመቶ ሃምሳው መጠናቀቁን ዋና መሐንዲስ አረጋግጠዋል፡፡

የአዲስ ሸክላ አክሲዮን ማኅበር ከጡብ ሌላ ለቤት ሥራ የሚስፈልጉትን ማንኛውም ዓይነት ሸክላዎችን የሚሠራ በጣም ዘመናዊ ሙሉ አውቶማቲክ የሸክላ መሥሪያ መኪናዎች ያሉት ትልቅ ድርጅት ነው፡፡

(ነሐሴ 11 ቀን 61 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን)

### ፪ ጭንቅላት ያለው ጥጃ ሞቶ ተወለደ

**ጉባ (ኢ.ዜ.አ.)** በባሌ ጠቅላይ ግዛት በገናሌ አውራጃ በዶዶላ ወረዳ ግዛት አቤና አንሻ በተባለው ቀበሌ ባለፈው ግንቦት ፳ ቀን ፷፩ ዓ/ም ንብረትነቷ የአቶ ጂሎ ጊጐ የሆነች ላም ልዩ ተፈጥሮ ያለው አንድ ወንድ ጥጃ ወለደች፡፡

ይኸው የተወለደው ጥጃ ሁለት ጭንቅላት፤ ፩ ጆሮ፤ ሁለት አፍ፤ ፩ ዓይን ሁለት ጭራ ያለው ሲሆን የእበት መጣያ ሥፍራ ደግሞ ድፍን መሆኑ ታውቋል። ጥጃው ከላይ በተጠቀሱት የአካል ክፍሎች ከሌሎች እንስሳት የተለየ ቢሆንም፤ እግሮቹና ብልቱ ትክክለኛውን የእንስሳት ተፈጥሮ የያዙ ናቸው፡፡

ይኸው ልዩ ተፈጥሮ ያለው ጥጃ ከመወለዱ በፊት በእናቱ ማህፀን ሞቶ ስለነበር በመንደር ወጌሻ ርዳታ የወጣ መሆኑን የአውራጃው ግዛት ዋና ጸሐፊ አቶ ሙላት ሙሉነህ ገለጠ፡፡

(ሰኔ 1 ቀን 1961 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካና ደቡብ ኮሪያ -"ትልቅ" የተባለለት ወታደራዊ ልምምድ ጀመሩ

አሜሪካ እና ደቡብ ኮሪያ ከዓመታት በኋላ "ትልቅ" የተባለ የጋራ ወታደራዊ ልምምድ እያካሄዱ መሆኑ ተሰማ። አገራቱ የጀመሩት ወታደራዊ ልምምድ ሰሜን ኮሪያ የጦር መሳሪያ ሙከራ ለማድረግ ከአጋሮቿ ጋር ዝግጁነቷን ለማጠናከር እየጣረች ባለበት ወቅት ነው ተብሏል፡፡

"ኡልቺ የነጻነት ጋሻ" ተብሎ የተሰየመውና በፈረንጆቹ መስከረም 1 የሚጠናቀቀው ዓመታዊ የበጋ ልምምድ የደቡብ ኮሪያ ፕሬዚዳንት የጋራ ወታደራዊ ልምምዶችን "መደበኛ" ለማድረግና ከሰሜን ኮሪያ ሊቃጣ የሚችልን ጥቃት ለመከላከል ቃል ከገቡ በኋላ የመጣ ነው።

ደቡብ ኮሪያ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ከተከሰተ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ የመንግስትን ዝግጁነት ለማሳደግ የተነደፈ ነው የተባለለትን የአራት ቀናት የኡልቺ ሲቪል መከላከያ ልምምዶችን ትናንት በተናጠል ጀምራለች።

ወታደራዊና የሲቪል ልምምዶች በፋብሪካዎችና በአቅርቦት ሰንሰለቶች ላይ ሊሰነዘሩ የሚችሉ ጥቃቶችን እና የጦርነት ሁኔታዎችን ለመመከት የአገሪቱን ዝግጁነት ለማሳደግ ያለመ መሆኑን ሬውተርስ በዘገባው አመላክቷል።

ፕሬዚዳንት ዮን በኮሪያ ልሳነ ምድር ሰላም ለማምጣት የሚደረገው ጥረት ደቡብ ኮሪያ ባላት ወታደራዊ አቋም ላይ እንደሚገነባ ለካቢኔ አባላቶቻቸው ባደረጉት ንግግር ገልጸዋል።

አሜሪካና ደቡብ ኮሪያ ልምምዶችን ለማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ ስልጠና ከጀመሩ በኋላ ሰሜን ኮሪያ ባለፈው ሳምንት ሁለት የክሩዝ ሚሳኤሎችን ከምዕራብ ጠረፍ ማስወንጨፏ ተገልጿል።

ሰሜን ኮሪያ በዚህ ዓመት በፍጥነት የሚሳኤል ሙከራዎችን ያደረገች ሲሆን፥ ሰባተኛውን የኒውክሌር ሙከራዋን በማንኛውም ጊዜ ለማካሄድ ዝግጁ መሆኗን የሴኡል ባለስልጣናት ተናግረዋል።

ደቡብ ኮሪያ ከጎረቤት ሰሜን ኮሪያ በኩል አለብኝ ለምትለው የሚሳኤል ጥቃት ስጋት የጥቃት ስጋቶችን ከመለየት ጀምሮ ወታደራዊ አቅሟን ለማሳደግ እንደምትሰራ አጽንኦት ሰጥታለች።

አሜሪካ፣ ደቡብ ኮሪያና ጃፓን በሃዋይ የባህር ዳርቻ የባለስቲክ ሚሳኤል የመከላከያ ልምምድ በቅርቡ ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡



## ኦዲንጋ የኬንያ ምርጫ ውጤትን ለማሰረዝ በፍርድ ቤት ክስ መሰረቱ

ራይላ ኦዲንጋ በቅርቡ የተካሄደውን ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ውጤት በመቃወም ለአገሪቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቀረቡ። የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሁለት ሳምንታት በፊት ተካሂዶ በነበረው ምርጫ በጠባብ የውጤት ልዩነት በወቅቱ ምክትል ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ መሸነፋቸው ታውጆ ነበር። ይሁን እንጂ ተቃዋሚ ፖለቲከኛው እና በወቅቱ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ የሚደገፉት ራይላ ኦዲንጋ፤ የምርጫ ውጤቱ ውድቅ እና ተቀባይነት የሌለው ነው ካሉ በኋላ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት እንደሚወስዱት መግለጻቸው ይታወሳል።

የራይላ ኦዲንጋ ጥምር ፓርቲ የሆነው አዚሚዮ የሕግ ቡድን የኬንያ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ውጤት ውድቅ ለማስደረግ ለፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረቡን አስታውቋል። የኬንያ ገለልተኛ የድንበር እና ምርጫ ኮሚሽን ከተሰጠው አጠቃላይ ድምጽ ዊሊያም ሩቶ



50.5 በመቶ እንዲሁም ራይላ ኦዲንጋ 48.8 በመቶ ማግኘታቸውን በመጥቀስ ዊሊያም ሩቶን ተመራጭ ፕሬዚዳንት ሲል ባለፈው ሳምንት አውጆ ነበር።

በአገሪቱ ሕግ መሠረት የምርጫው ውጤት ከታወቀ በኋላ ባሉት ሰባት ቀናት ተቃውሞ ያለው አካል ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታውን ማሰማት አለበት። በዚህም መሠረት ነው ኦዲንጋ ውጤቱን አልቀበለውም ያሉትም ምርጫ በተመለከተ በታዋቂ የሕግ ባለሙያዎች አማካይነት አቤቱታ ያቀረቡት።

የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ዋፉላ ቼቡካቲ ዊሊያም ሩቶን ተመራጭ ፕሬዚዳንት ብለው ያውጁ እንጂ ሁሉም የኮሚሽኑ አባላት በምርጫ ውጤቱ አልተስማሙም። የኬንያን ፕሬዚዳንታዊ ምርጫን ያስፈጸመው ኮሚሽን 7 ኮሚሽነሮች ያሉት ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል አራቱ በፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ውጤቱ አለመስማማታቸውን በሰጡት መግለጫ ተናግረው ነበር።

ኮሚሽነሮቹ የምርጫው አካሄድ "ግልጽነት የጎደለው በመሆኑ፣ ለውጤቱ ኃላፊነት መውሰድ አንችልም" ማለታቸው ለራይላ ኦዲንጋ የፍርድ ቤት ክርክር ኃይል የሚሰጥ ይሆናል ተብሏል። የኬንያ ጠቅላይ ፍርድ የቀረበውን ክስ መርምሮ በሁለት ሳምንታት ውስጥ ብይን መስጠት አለበት። ፍርድ ቤቱ ከአምስት ዓመት በፊት ተካሂዶ የነበረውን የምርጫ ውጤት ውድቅ ካደረገ በኋላ ኬንያ ዳግም ምርጫ ማካሄድ ግድ ብሏት ነበር።

እአአ 2017 ላይ በተካሄደውን ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ አሁን ሥልጣን ላይ ባሉት ኡሁሩ ኬንያታ ተሸንፈው የነበሩት ራይላ ኦዲንጋ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ውስደው የምርጫ ውጤቱን 'ውድቅ እና ተቀባይነት የሌለው' አስብለው ነበር። በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በ60 ቀናት ውስጥ በተደረገው ዳግም ምርጫ ኦዲንጋ እራሳቸውን ካገለሉ በኋላ ኡሁሩ ኬንያታ ለሁለተኛ የሥልጣን ዘመን ማሸነፍ ችለው እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ማክሰኞ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# "ምርጫውን ካሸነፍኩ ለእግር ኳሱ ትንሳኤ እሰራለሁ"

**- አቶ መላኩ ፈንታ**

**ቦጋለ አበበ**

በሳምንቱ መጨረሻ ሊካሄድ በታቀደው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ስፖርቱን ለቀጣይ አራት አመታት የሚመሩ ግለሰቦች ለፕሬዚዳንትነትና ለስራ አስፈጻሚነት የሚያደርጉት የምርጫ ፉክክር ይጠበቃል። የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴውም ባለፈው ሳምንት ለፕሬዚዳንትነት የሚፎካከሩ ሶስት የመጨረሻ እጩዎችን ይፋ ማድረጉ ይታወቃል። በዚህም ባለፉት አራት አመታት ፌዴሬሽኑን ሲመሩ የቆዩት አቶ ኢሳያስ ጂራ ከኦሮሚያ ክልል ተወክለው ለፕሬዚዳንትነት የሚፎካከሩ ሲሆን፣ አቶ መላኩ ፈንታ ከአማራ ክልል እንዲሁም አቶ ቶኩቻ አለማየሁ ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የፕሬዚዳንታዊ ምርጫው እጩ ሆነው መቅረባቸው ይታወሳል። ከፕሬዚዳንታዊ እጩዎች መካከል የአገልግሎት ዘመናቸውን አጠናቀው ዳግም ለመመረጥ እየተፎካከሩ የሚገኙት አቶ ኢሳያስ ባለፈው ሳምንት በእሳቸው የአስተዳደር ዘመን ፌዴሬሽኑ ላይ እየቀረቡ ለሚገኙ ትችቶች ምላሽ የሰጡ ሲሆን ሌላኛው ተፎካካሪ አቶ መላኩ ፈንታ ደግሞ ትናንት ምርጫውን በተመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል።

አቶ መላኩ ፋንታ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫውን ካሸነፉ ሊሰሯቸው ያሰቧቸውን የትኩረት አቅጣጫዎችን በመግለጫው ላይ ይፋ ያደረጉ ሲሆን፣ ከዚህ በፊት የተደረጉ ምርጫዎችን በተመለከተ ብዙ ብልሹ አሠራሮች መኖራቸውን በሰነድና በሰው ማስረጃ አረጋግጫለሁ ብለዋል። ይህ ነገር ለእግር ኳሱ እድገት ስለማይበጅም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊታገሉት እንደሚገባ አሳስበዋል። "ሃሳብ እንጂ ኔትወርክ፣ ገንዘብ፣ አካባቢና ዘር ተኮር ምርጫ መቆም አለበት" ያሉት



**አቶ መላኩ ፈንታ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫውን ካሸነፉ ሊሰሯቸው ያሰቧቸውን የትኩረት አቅጣጫዎችን በሰፊው አንስተዋል፣**

አቶ መላኩ በተለይም በምርጫው ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸው የጉባኤ አባላት በገንዘብ ከመገዛት መውጣት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

ምርጫውን እንደሚያሸንፉ ያላቸውን እምነት የገለፁት አቶ መላኩ፣ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫውን ካሸነፉ ሊሰሯቸው ያሰቧቸውን የትኩረት አቅጣጫዎችን በሰፊው አንስተዋል። እግር ኳስ በጠንካራ ቢዝነስ ሞዴል ከተመራ ትልቅ አገራዊ ተፅዕኖ እንደሚፈጥር የዓለም አቀፍ ተሞክሮን አንስተውም ሃሳብ ሰጥተዋል።

"ኢትዮጵያ የካፍ መስራች ብትሆንም ዓለም እየተጠቀመበት ካለው ትልቅ የእግር ኳስ አቅም መጠቀም አልተቻለም" የሚሉት አቶ መላኩ፣ በኢትዮጵያ ያለውን ሰፊ የእግር ኳስ አቅም፣ ወጣቶችን፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና ሌሎችንም በቅንጅትና በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ ዓለም ወደ ደረሰበት ደረጃ በቀላሉ መድረስ እንደሚቻል አስረድተዋል።

"የኢትዮጵያን እግር ኳስ ትንሣኤ እውን ለማድረግ ሁላችንም ለለውጥ ዝግጁ መሆን አለብን፤ እኔም፣ አንተም፣ አንቺም፣ እናንተም፣ ሁላችንም ይህን የለውጥ ሃሳብና ተነሳሽነት በአመራርነት ለማቀጣጠል፣ ከፊት ሆኖ ለምራትና በለውጥ ለለወጥ እንነሳ" ያሉት አቶ መላኩ ፋንታ ቻይ በሥራ አመራር ቦርድ መሪነትና በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ በመሳተፍ በርካታ ስኬቶችን እና ተጠቃሽ ውጤቶችን ያስመዘገቡ ሲሆን፤ አሻራቸውን ባሳረፉባቸው ተቋማት ሁሉ አዳዲስ የለውጥና ማሻሻያ ሃሳቦችን በማመንጨትና በመተግበር ይታወቃሉ። በአሁኑ ሰዓት የአማራ ልማት ማኅበር ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ መላኩ ፋንታ መንግስት በተሰጣቸው የሥራ ኃላፊነት በርካታ ተቋማትን መርተዋል። ከነዚህ መካከል በኢትዮጵያ የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚኒስትር ማዕረግ ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሆነው ማገልገላቸው ይታወሳል።

አቶ መላኩ ፈንታ በሥራ አመራር ቦርድ መሪነትና አባልነት በርካታ ተቋማትን ያገለገሉና በማገልገል ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ቦርድ ሰብሳቢ፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ቦርድ ሰብሳቢ እንዲሁም በቅርቡ ወደ ሥራ የገባው አማራ ባንክ ከምሥረታው ጀምሮ የቦርድ ሰብሳቢ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ እግር ኳሱ ከቅርብ አመታት ወዲህ ስኬታማ መሆኑን ያስመሰከረው የፋሲል ከነማ የስፖርት ክለብም የሥራ አመራር ቦርድ አባል ናቸው። ይህን ከፍተኛ ልምድና ውጤታማ ተሞክሮ በእግር ኳሱ መድረክ ለመጠቀምና በለውጥ ሃሳብ ትግበራ የእግር ኳስ ፌዴሬሽንን በፕሬዚዳንትነት ለመምራት ጠንካራ ተፎካካሪ ያደርጋቸዋል ተብሎ ይጠበቃል።

"ስፖርት በተለይም እግር ኳስ የሕዝብ፣ ለሕዝና በሕዝብ የሚከወን እንደመሆኑ በተቋማዊ ለውጥ ትግበራ የሚፈለገው ተጨባጭ ውጤት እንዲገኝ ለውጡ ባለድርሻዎችን ሁሉ ያካተቱ የሚከተሉት መሠረታዊ መርሆዎች ይኖሩታል" ብለው ወደ ምርጫው ፉክክር የገቡት አቶ መላኩ በአዝጋሚ ሂደቶች በተገኙና በሚገኙ አንዳንድ ውጤቶች በመርካት ሳይሆን ሁለንተናዊ የሆነ ተቋማዊ ለውጥ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

አቶ መላኩ ምርጫውን ካሸነፉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በጋራ የሚሳተፉበትና በተለይ መንግሥት፣ የግሉ ዘርፍና ሕዝቡ ለእግር ኳሱ ትንሣኤ በጋራ እንዲሰሩ የማስቻል አላማ እንዳላቸው ገልጸዋል። የመልካም አስተዳደር እጦት፣ በተለይም የሙስና ችግር የስፖርቱ ውድቀት ዐብይ ምክንያት በመሆኑ መልካም አስተዳደርንና ተጠያቂነትን ማስፈን፣ ለስፖርቱ እድገት ቀጣይነት አስተማማኝ የገቢ ምንጭ እንዲኖር ስፖርቱን በቢዝነስ መርህ መምራት፣ ስፖርቱ ከሁሉም፥ ለሁሉም እንዲሆን ተደራሽነትን ማስፋት፣ ነፃና ገለልተኛ እንዲሆን ለማስቻልም እንደሚሰሩ አብራርተዋል።

ስፖርቱ በእውቀት እንዲመራ እያንዳንዱ ተግባር ብቃት ባለው ባለሙያ እንዲመራ በዘርፉ በጥናትና ምርምር የታገዘ ሥራ የማከናወን ፍላጎት እንዳላቸውም ጠቁመዋል። ተቋማዊ አቅሙ የዳበረ፣ በኢትዮጵያውያን ሁሉ ቅቡል የሆነና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነቱ ከፍ ያለ የእግር ኳስ ፌዴሬሽን የመገንባት ራእይና አላማ እንዳላቸውም ተናግረዋል።

## ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
## በየሳምንቱ የሚታተም

# የ‹‹ደራሽ ለመርካቶ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር›› ስኬታማ ጉዞ

**በዳኛቸው ቀደማቸው**

መንግሥት በነደፈው የነፃ ገበያ ሥርዓት አገራችን የተቀበለችው የዓለም አቀፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት መርህ በትክክል መተግበር ከተጀመረ ወዲህ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴ አንዱ የልማት አማራጭ ሆኗል። ለዚሁም ዜጎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት፣ ያለባቸውን የጋራ ችግር በጋራ ለመወጣትና የገበያ ዋጋ መናርን ለመቆጣጠር የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተዋል። የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት በዓለማችን ለብዙ ኅብረት ሥራ ማህበራት መመስረት ፈር ቀዳጆች ናቸው። በተለይ በአውሮፓ የኢንዱስትሪ አብዮትን ተከትሎ በተፈጠረው የኑሮ ቀውስ ችግሮችን በመደራጀት ለመፍታት ግንባር ቀደም ሚና ነበራቸው። በተለያዩ አገራት የሚገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት የበርካታ አገራት የቀውስ መፍቻ መሳሪያና የህዝብ አለኝታነታቸውን አስመስክረዋል።

አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ምክንያቶች የተከሰተው የገበያ ቀውስ በሸማቹ ህብረተሰብ ላይ የሸቀጣሸቀጦችና የምግብ ፍጆታ እቃ ዋጋ ንረትን አስከትሏል። ስለሆነም መንግሥት በተለይ በከተሞች አካባቢ የዋጋ ንረቱን ለመከላከል የችግር መፍቻና የዘለቄታዊ ልማት አጋር አድርጎ የወሰዳቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ቀዳሚ ተጠቃሽ ናቸው። ከነዚህ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መካከል የደራሽ መርካቶ ኃላፊነቱ የተወሰነ ሁለገብ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር አንዱ ነው። ኅብረት ሥራ ማኅበሩ የምግብ ፍጆታ ዋጋ መናር ያመጣውን የገበያ ቀውስ ለመቋቋም ለሸማቹ ኅብረተሰብ የተለያዩ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ከማቅረቡም ባሻገር ለአካባቢው ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለ

**አሁን ላይ በሸማች ዘርፍ የሚገኙ 11 ሱቆችን፣ ሰባት የመዝናኛ ተቋማትን፣ ሁለት ሱፐር ማርኬቶችን፣ ሦስት ወፍጮ ቤቶችንና ክሊኒክ፣ ስፖርት ቤት፣ የሻወር ቤትና የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡና የሚከራዩ ሱቆችን በመያዝ ለህብረተሰቡ ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡**

አንጋፋ ዩኒየን ነው።

ደራሽ መርካቶ ኃላፊነቱ የተወሰነ ሁለገብ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር በ2007 ዓ.ም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 አስተዳደር ክልል ውስጥ የነበሩ አራት መሰረታዊ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት ተዋህደው የመሰረቱት ማህበር ነው። ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ሲቋቋም የነበሩት የአባላት ብዛት ሶስት ሺ 427 ነበሩ። በወቅቱ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ካፒታል እና 36 ሠራተኞችን በመያዝ ነበር በመላው አባላት ስምምነት ወደ ሥራ የገባው። አሁን ላይ በሸማች ዘርፍ የሚገኙ 11 ሱቆችን፣ ሰባት የመዝናኛ ተቋማትን፣ ሁለት ሱፐር ማርኬቶችን፣ ሦስት ወፍጮ ቤቶችንና ክሊኒክ፣ ስፖርት ቤት፣ የሻወር ቤትና የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡና የሚከራዩ ሱቆችን በመያዝ ለህብረተሰቡ ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። በአሁኑ ሰዓት የአባላት ቁጥር ወደ አራት ሺ 948 ያደገ ሲሆን በአጠቃላይ 11ሺ 97 የዕጣ ሽያጭ አካሂዷል።

ደራሽ ለመርካቶ ኃላፊነቱ የተወሰነ ሁለገብ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር የአባሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ለመፍታት በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የተቋቋመ የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበር እንደመሆኑ ዓላማውን በጥሩ ሁኔታ እያሳካ የሚገኝ ነው። ማህበሩ አባላቱን ተጠቃሚ እያደረገ ያለና በቀጣይም በሚሠራው ሁሉን አቀፍ ሥራ ሕብረተሰቡን እያገለገለና ጠንካራና ቀጣይነት ያለው ሸማች ኅብረት ሥራ የመፍጠር ተልዕኮ ሰንቆ እየሠራ ነው።

የትርፍ ክፍፍልን በተመለከተ በሸማች ዘርፍ አክሲዮን ገዝተው የማህበሩ አባል ለሆኑ የወረዳው ነዋሪዎች ከ2009 እስከ 2012 ዓ.ም ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚጠጋ ብር አከፋፍሏል። በ2013 ዓ.ም በጀት ዓመት ከ275 ሺ ብር በላይ ለአባላት እንደ እጣ ድርሻቸው ሰጥቷል። ማህበሩ የሂሳብ ምርመራን መሰረት በማድረግ በየጊዜው የሂሳብ አያያዝ ስርዓቱን በማሻሻልና ለኦዲት ምቹ በማድረግ የመረጃና የሂሳብ አያያዙን በማዘመን ላይ ይገኛል።

ደራሽ ለመርካቶ ኃላፊነቱ የተወሰነ ሁለገብ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር በሸማች ዘርፍ እና በመዝናኛ ተቋማት ያለውን የሂሳብ ሰነድ እስከ 2013 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ አስመርምሯል። በመሆኑም በነዚህ አመታዊ የሂሳብ ምርመራ ኦዲት መሰረት የሂሳብ አያያዝ ክፍተት መሙያ አስተያየቶችን ተቀብሎ በፍጥነት ተግባራዊ በማድረግ የድርጅቱን የጀርባ አጥንት የሆነውን የሂሳብ አያያዝ ግልፅነትና ተጠያቂነት በተሞላበት መልኩ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ከማህበሩ የሥራ ሪፖርት መገንዘብ ተችሏል። ማንኛውም ሸማች አክሲዮኑን በመግዛት የሸማቾች ህብረት ሥራን መቀላቀል ስለሚችል የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የሚቀላቀሉ አባላት ቁጥር እለት በዕለት እያደገ ይገኛል።

የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠትና ተጠቃሚ ማህበረሰብን ማገልገል ተቀዳሚው ተልዕኳቸው ነው። የማኅበራቱ ተቀዳሚ ዓላማ የአባላት ፍላጎቶችን ማሟላት እንጂ ትርፍ ማስገኘት ስላልሆነ አባሎቻቸውን በዝቅተኛ ወጪ ማገልገል ይገባቸዋል። በደራሽ ለመርካቶ ሸማች ኅብረት ሥራ ማህበርም ያለው እውነታ ይህ ነው።

የደራሽ ለመርካቶ ሸማች ኅብረት ሥራ ማህበር እስካሁን የደረሰበትን የእድገት ጉዞ ለማስቀጠል የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ አዘጋጅቶ በመንቀሳቀስ አመርቂ ውጤት ለማስመዝገብ እየተጋ ያለ የህዝብ ተቋም ሲሆን፣ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ በ2015 በጀት ዓመት በእቅዱ ከያዛቸው ትልሞች መካከል የተቋሙን የውስጥ አቅም ለማጠናከር የቦርድ አባላት፣ የተቀጣሪ ሠራተኞች እና የተለያዩ ተግባራትን የሚከውኑ የንዑስ ኮሚቴ አባላትን አቅም ከማጎልበት ባሻገር የአገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ ለማዘመን እና ተደራሽነቱን ለማስፋት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ